# Institutional Independence of Federal Courts in Ethiopia: Observations

Aron Degol ♣

## Abstract

As one of the three organs of government, the structure and powers of the judiciary are enshrined in the 1995 FDRE Constitution. Articles 78 to 81 of the FDRE Constitution and other laws deal with the independence of the judiciary, judicial powers, jurisdiction of courts and appointment of judges. The principles enshrined in these laws include the *independence of the judiciary* which has two dimensions, i.e., *individual/professional independence* of judges and *institutional independence of courts* from other organs of the government. This article focuses on the legal regime and the practices with regard to the *institutional independence* of federal courts in Ethiopia that are inconsistent with the constitutional guarantee of judicial independence which includes empowerment in the preparation of budget, the process of budget approval, level of autonomy in using revenue generated through court fees, independent administration of support staff at courts, procurement processes and property administration. The article analyzes the relevant laws and discusses comparative experience on these avenues of concern and calls for due attention to the gaps that should be addressed.

## Key terms:

Judicial independence · Federal courts · FDRE Constituiton · Ethiopia

**DOI** http://dx.doi.org/10.4314/mlr.v14i2.5

This article is licensed under a Creative Commons Attribution-NonCommercial-NoDerivs (CC BY-NC-ND)

**Received**: 26 July 2020 **Accepted**: 14 December 2020

**Suggested citation**:

Aron Degol (2020), 'Institutional Independence of Federal Courts in Ethiopia: Observations' (in Amharic), 14 *Mizan Law Review* 2: 310-340

♣ Aron Degol (LLB, LL.M, MBA), Lecturer, St. Mary's University, Email: arondegol416@gmail.com
ORCID: https://orcid.org/0000-0002-6035-2222

# የዳኝነት ተቋማዊ ነፃነት በኢትዮጵያ ፌደራል ፍርድ ቤቶች፣ አጭር ምልከታ

አሮን ደጎል♣

"ፈታሒ ይኩን ግዑዘ እስመ ዘኢኮነ ሥሉጠ ላዕለ መግቦተ ነፍሱ ኢይትከሀሎ ከመ ይመግብ ካልአኒሁ"

"ዳኛ ነፃነት ያለው ይሁን። ራሱን ለማስተዳደር ሥልጣን ያለው ያልሆነ ሰው ሌሎቹን ሊያስተዳድር አይቻለውምና"

ፍትሐ ነገሥት አርባ ሦስተኛ አንቀጽ ቁ. 1፣ 420

*"A Judge must be a free man, because he who has no power over himself has no power over others"*

Fetha Negest CH. XLIII Sec. I


## አህጽሮተ ይዘት (Abstract)

*መንግሥትን ከሚያቋቁሙት ሦስት ሕገ መንግሥታዊ አካላት መካከል አንዱ የሆነው የዳኝነት ተቋም በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት ከአንቀጽ 78 እስከ 81 ባሉት ድንጋጌዎች እና በሌሎች አዋጆች የተደራጀ መሆኑ ይታወቃል። በተለይም የዳኞች ግለሰባዊና ውሳኔአዊ ነፃነት እንዲሁም ተቋማዊ ወይም አስተዳደራዊ ነፃነት በሕገ መንግሥቱም ሆነ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 በጉልህ የተቀመጠ መርህ ነው። ነገር ግን በተለይም ተቋማዊ ወይም አስተዳደራዊ ነፃነቱን በተመለከተ በአተገባበር ላይ ሕገ መንግሥቱን በግልጽ የሚጣረስ አሠራር ይስተዋላል። በበጀት አወሳሰን፣ አጸዳደቅና አጠቃቀም፣ በውስጥ ገቢ አጠቃቀም፣ በድጋፍ ሰጪ የሰው ኃይል አስተዳደር እንዲሁም በግዢና ንብረት አስተዳደር ላይ ፌደራል ፍርድ ቤቶች አሁንም ድረስ ኢ-ሕገ መንግሥታዊ በሆነ መልኩ በአስፈጻሚው ቁጥጥር ሥር እንዲሆኑ ተደርጓል። ይህ ኢ-ሕገ መንግሥታዊ አሠራር በምን መልኩ የፌደራል ፍርድ ቤቶችን ነፃነት እየገደበ እንዳለና በምን መልኩ ሊፈታ እንደሚገባው ከሌሎች ሀገራትን ተሞክሮና ዓለም አቀፍ መርሆችን ከያዙ ሰነዶች አንፃር በዚህ ጽሁፍ ለመዳሰስ ተሞክሯል።*


**ቁልፍ ቃላት፡-**

*የዳኝነት ነፃነት፣ የፌደራል ፍርድ ቤቶች፣ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት፣ ኢትዮጵያ*

---

♣ አሮን ደጎል (ኤል ኤል ቢ፣ ኤል ኤል ኤም፣ ኤም ቢ ኤ), ሌክቸረር፣ ቅድስት ማርያም ዩኒቨርሲቲ፣
ቃላትንና ዐረፍተ ነገሮችን በማረም ያገዙኝን ወ/ሮ ፍቅሬ አያሌውና አቶ አስቻለው አሻገሬ (ረ/ፕሮፌሰር) ማመስገን አወዳለሁ።
ኢሜይል:- arondegol416@gmail.com
ORCID: https://orcid.org/0000-0002-6035-2222

## *መግቢያ*

ፍርድ ቤቶች ሕገ መንግሥታዊ ተልዕኳቸውን ለመወጣት ሊመሩባቸው ከሚገቧቸው መሠረታዊ መርሆች አንዱ የዳኝነት ነፃነት ነው፡፡ የዳኝነት ነፃነት ሲባል ፍ/ቤቶች የማንኛውም አካል እንዲሁም ማንኛውም ዓይነት ጣልቃ ገብነት ሳይኖርባቸው ውሳኔ የሚሰጡበት ጽንሰ ሓሳብ ነው፡፡ የዳኝነት ነጻነት በዋነኛነት ተቋማዊና ግለሰባዊ ተብሎ ይከፈላል፡፡ ተቋማዊ ነፃነት በተቋም ደረጃ ፍርድ ቤቶች አስተዳደራቸውና መዋቅራቸው ከማንም አካል ተጽእኖ ነፃ መሆን እንዳለበት የሚደነግግ ሲሆን፣ ግለሰባዊ ነፃነት ማለት ደግሞ ዳኞች በግላቸው ማንኛውም አካል ጣልቃ ሳይገባባቸው ውሳኔ የመስጠት ሥራቸውን የሚሠሩበት ሥርዓት ነው፡፡ የዳኝነት ነፃነት መርህን በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ በቂ የሕግ ማዕቀፍ (legal framework) መኖር አለመኖሩን፣ የመርሁ ምንነትና ገፅታዎች፣ የመርሁ አስፈላጊነት እነዲሁም የመርሁ ተግባራዊ አፈፃፀም ግልፅ መደረግ አለባቸው፡፡ በተለይም የዳኝነትን ተቋማዊ ነፃነት በሕገ መንግሥቱ መንፈስ መሠረት ተግባራዊ ለማድረግና ጥራትና ቅልጥፍናን ባገናዘበና ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ሕግ ተርጓሚው አካል ኃላፊነቱን እንዲወጣ ለማስቻል፣ የፍርድ ቤቶችን የሰው ኃይል፣ ገንዘብና ንብረት አስተዳደር በተመለከተ ውሳኔ መሰጠት ያለበት በራሳቸው በፍርድ ቤቶች ብቻ ነው፡፡ በተለይም የአስፈጻሚው እጅ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እንዳይገባበት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በመዋቅርም ሆነ በተግባር በሁለት መሠረታዊ ዘርፎች የተከፈሉ ናቸው፡፡ አንደኛው ዘርፍ የፍርድ ቤቶች ዓላማ አስፈጻሚ የሆነው ዋነኛው አካል የዳኝነት ዘርፍ (the core/main judicial wing/staff) ሲሆን የፍርድ ቤቱ ተልዕኮ የሆነውን ባለጉዳዮችን አከራክሮ ውሳኔ የሚሰጡትን ዳኞችን የሚመለከት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ድጋፍ ሰጭ (support staff/wing) ተብሎ የሚታወቀውን አስተዳደራዊ ዘርፍ ነው፡፡ ይህ ዘርፍ ፍርድ ቤቶች ተልዕኳቸውን ለማሳካት የሚያስፈልጉ አስተዳደራዊ ድጋፎችን የሚያሟሉና በተለያየ መልክ ድጋፍ የሚያደርጉ ሠራተኞችን ያቀፈ ነው፡፡

ዋነኛው የዳኝነት ዘርፍ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 79(6) እና በተሻሻለው የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 684/2002 አንቀጽ 6 መሠረት የዳኞችን ደመወዝ፣ ዲሲፕሊን፣ ጥቅማ ጥቅም፣ ምደባ፣ ዝውውርና ሌሎች ጉዳዮችን በፌዴራሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አማካኝነት የፍርድ ቤቶችን ነፃነት ባማከለ መንገድ የሚፈጸም ነው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ፣ የድጋፍ ሰጪ ክፍሎች ስምሪትና አስተዳደር የሚመራው በመደበኛው የሲቪል ሰርቪስ ሥርዓት ነው፡፡ ይህም ከዳኝነት ተቋማዊ ነፃነት ጋር በሚፃረር መልኩ ተቋሙን ለሁለት በመከፋፈል፣ ለዳኝነት አገልግሎት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በሚመለከት ኃላፊነት ያላቸውን ሥራ ክፍሎች ከዳኝነት ዘርፍ አውጥቶ በአስፈፃሚው አካል እንዲተዳደሩ አድርጓል፡፡ የበጀት ጥያቄ አቀራረብ፣ አፈቃቀድና አደላደል፣ የግዢ አፈጻጸምና ንብረት አወጋገድ እንዲሁም ሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮችም በፍርድ ቤቶች በራሳቸው የሚወሰኑ ሳይሆኑ፣ በተለያዩ የአስፈጻሚ አካላት ውሳኔ የሚሰጥባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ ይህም በሕገ መንግሥቱ ከተረጋገጠው የዳኝነት ነፃነት መርህ ጋር የሚጣረስ ነው፡፡ ምንም እንኳን ከዚህ በፊት የፍርድ ቤቶችን ሥልጣን የሚሸረሽሩ ሕግጋት ወጥተው ሥራ ላይ የዋሉ ቢሆንም የዚህ ጽሁፍ ዋነኛ ዓላማ የዳኝነት ተቋማዊ ነፃነት መሠረታዊ መርሆዎች፣ ዓለም ዓቀፍ መለኪያዎችና ተሞክሮዎችን በመዳሰስ በኢትዮጵያ በተለይም በፌደራል ፍ/ቤቶች ያለውን ሁኔታ በአጭሩ ማሳየት ነው፡፡

## 1. የዳኝነት ነፃነት ምንነት ጠቀሜታና ገጽታዎች

የዳኝነት ነፃነት ምንነትና ጠቀሜታ ወይም አስፈላጊነት ብዙ የተባለበት ጉዳይ ነው፡፡ የዘርፉ ምሁራን በተለያየ መንገድ ለዚህ መርህ ትርጉም ለመስጠት ሞክረዋል፡፡ መርሁ በብዙ ሀገራት ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቶች ውስጥም ቦታ የተሰጠውና ጥበቃ የተደረገለት ነው፡፡ ፕሮፌሰር ሮዘን እንደገለጹት የዳኝነት ነፃነት ሲባል ዳኞች ጉዳዮችን/ክርክሮችን ማስረጃዎችን መርምረውና መዝነው በሕግና በርትዕ መሠረት ከማንኛውም ተጽእኖ፣ ሙገሳ፣ መንግሥታዊም ሆነ ግላዊ ጣልቃ ገብነቶች ነፃ ሆነው የመወሰን አቅም ማለት ነው፡፡[1] በተመሳሳይ ሁኔታም የዳኝነት ነፃነት ሲባል ዳኞች ከማንኛውም መንግሥታዊ/ ውጫዊ ቁጥጥር፣ ግፊትም ሆነ ስጋት ነፃ በመሆን የዳኝነት ሥራቸውን የሚከውኑበት ሥርዓት ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡[2] በአጠቃላይ የዳኝነት ነፃነት ማለት ዳኞች ካለምንም ውጫዊና ግላዊ ጣልቃ ገብነት፣ ተፅዕኖና ግፊት የቀረበላቸውን ጉዳይ ሕጉንና ማስረጃ ብቻ መሠረት በማድረግ ለመወሰን ያላቸውን ነፃነት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

በእርግጥ የዳኝነት ነፃነት የሚያጠነጥነው በዳኞች ግላዊ/ውሳኔያዊ ነፃነት ላይ ነው፡፡ ሆኖም የዳኝነት ነፃነት በዳኞች ግላዊ/ውሳኔያዊ ነፃነት ብቻ የተወሰነና በቂ ነው ብሎ ማሰብ ስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም ዳኞች ግላዊ/ውሳኔያዊ ነፃነታቸውን ተጠቅመው ፍትሓዊ ውሳኔ ሊሰጡ የሚችሉት ይህንን ለማድረግ የሚያስችል ጠንካራ የዳኝነት ተቋም ውስጥ መሥራት ሲችሉ ብቻ ነው፡፡ ይህም ማለት በዘመናዊ የዳኝነት ነፃነት ጽንሰ ሓሳብ መሠረት የዳኝነት ነፃነት ባለቤት ዳኞች ብቻ ሳይሆኑ ፍ/ቤቶችንም እንደ ተቋም የሚያጠቃልል ነው፡፡ የዳኝነት ነፃነት ሲባል ፖለቲካዊ ዓላማ የሌላቸው፣ ጉዳዮችን ገለልተኛ በሆነ መንገድ የሚያስተናግዱና በአንድ ተቋም ሥር በመሆን የመንግሥትን እንቅስቃሴ ሕጋዊነት ተቋማዊ በሆነ መንገድ የሚቆጣጠሩ ዳኞች ያሉበት ሥርዓት ነው የተባለውም ለዚህ ነው፡፡[3]

በአጠቃላይ ከዚህ መረዳት የምንችለው የዳኝነት ነፃነት ባለቤቶች ዳኞችና ፍ/ቤቶች መሆናቸውንና የዳኝነት ነፃነት ቀደም ሲል ይሰጠው የነበረው ትርጉምና በአሁኑ ዘመን ያለው አረዳድ አንድ ዓይነት አለመሆኑን ነው፡፡ ሀገሮችም ከሚከተሉት የሕግ ሥርዓትና ሊያሳኩት ካሰቡት ግብ አኳያ ለዳኝነት ነፃነት የተለያዩ ትርጉሞች ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ነፃ የሆነ ፍ/ቤት የሕግ በላይነት መከበሩን የሚያሳይ መሠረታዊ ገጽታና ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መኖር ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ዋነኛ ባህሪ የሰብዓዊ መብቶች መከበርና መረጋገጥ ሲሆን መብቶችና ነፃነቶቹ በሕገ መንግሥት ወይም በሌላ ሕግ መደንገጋቸው ብቻ በራሱ ለመብቶች መረጋገጥ ዋስትና ሊሆን አይችልም፡፡ እነዚህ መብቶች እውን የሚሆኑት እና የሕግ የበላይነት

[1] Keith S. Rosenn (1987). *The Protection of Judicial Independence in Latin America*, International American Law Review Vol. 19, No. 1.

[2] Penny J. White (2002). "Judging Judges: Securing judicial independence by use of judicial performance evaluation", *Fordham Urban Law journal*, Vol. 29

[3] Christopher Larkins (1996), "Judicial independence and Democratization: A theoretical and conceptual analysis", *American Journal or Comparative Law*, Vol. 44 # 4

የሚከበረው ነፃነቱ የተረጋገጠ የዳኝነት አካል ወይም ፍ/ቤት ሲኖር ብቻ መሆኑን ብዙዎች ይስማማሉ፡፡[4]

ከዚህ በተጨማሪም የሌሎቹን የመንግሥት አካላት የሥልጣን አጠቃቀም ከሰብዓዊ መብቶች አከባበር ጋር እንዲያያዝ በማድረግ የመንግሥት ሥልጣን ገደብ እንዲኖረውና ከገደቡ እንዳያልፍ ቁጥጥር በማድረግ ረገድ የፍ/ቤቶች ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ለዚህም ይመስላል ከዛሬይቱ ሀገረ አሜሪካ መሥራች አባቶች መካከል አንዱ የሆኑት ሃሚልተን በፌደራሊሰት ጽሑፍ ትንታኔ ውስጥ የመንግሥትን ሥልጣን በመቆጣጠርና የዜጎችን መብት በማስከበር በኩል ከፍርድ ቤቶች በላይ የተሻለ ሥርዓት ማሰብ አይቻልም በማለት የገለፁት፡፡[5]

ነፃነት የሌለው ፍ/ቤት የሰዎችን መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች እንዲረጋገጥ ሊያደርግ አይችልም፡፡ በዜጎችና በመንግሥት እንዲሁም በሰዎች መካከል ባለው ግንኙነት ሳቢያ የሚነሱ የፍትሐ ብሔር ወይም ወንጀል ክርክሮችን ገለልተኛና ነፃ ሆኖ እልባት ሊሰጥ የሚችል ፍ/ቤት በሌለበት የሕግ በላይነት ሊረጋገጥ አይችልም፡፡ የሕግ የበላይነት ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ደግሞ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና መልካም አስተዳደር እውን ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ሰላምና ዘለቄታዊነት ያለው ልማትም ዋስትና አይኖረውም፡፡

በአጠቃላይ የዳኝነት ነፃነት ጠንካራ የዳኝነት ተቋም እንዲኖር ቁልፍ መሣሪያ ብቻ ሳይሆን ኅብረተሰብአዊ ግብን፣ የሰው ልጆች ነፃነትን፣ ዘላቂ ልማትንና ብልጽግናን ለማረጋገጥ እንደዚሁም ለኢንቬስትመንትና ለአጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት መሠረት ነው፡፡ ሕዝቡና ባለሀብቱ በፍርድ ቤቶችና በዳኞች ላይ እምነት እንዲኖረው በአንድ አገር ውስጥ የዳኝነት ነፃነት መስፈንና መረጋገጥ ወሳኝ ነው፡፡[6] የዳኝነት ነፃነትን በርካታ ምሁራን በተለያየ መንገድ ከፍለው ያዩታል፡፡ አንዳንዶቹ ግለሰባዊ፣ ውስጣዊና ተቋማዊ በማለት ለሦስት ከፍለው ሲመለከቱት[7] በአብዛኛው ግን ይህንን ጽንሰ ሐሳብ ምሁራን በሁለት ዋና ዋና ገጽታዎች ከፍለው ይመለከቱታል፡፡[8] የመጀመሪያው ግላዊ ወይም ግለሰባዊ ነፃነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተቋማዊ ነፃነት ነው፡፡

### 1.1 ግላዊ/ግለሰባዊ ነፃነት

የዳኞች ግላዊ ነፃነትን በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡ እነዚህም ውሳኔያዊ ነፃነት (decisional/functional independence) እና ግላዊ ነፃነት (personal/private

---

[4] Das, Cyrus and Chandra, K., (Eds.), (2003), *Judges and Judicial Accountability*, Universal Law Publishing Co. Pvy. Ltd, New Delhi, India, p. 89

[5] Alexander Hamilton, The Federalist No. 78 (cited in Das, Cyrus and Chandra, K., Eds. Id., p. 89),

[6] ዝኒ ከማሁ

[7] Shimon Shetreet, (1994). *Justice in Israel: A study of the Israeli Judiciary*, Martinus Nijhoff publishers, Boston,

[8] በተጨማሪም የዳኝነት ነጻነት ውጫዊና ውስጣዊ *(Internal and External*) ወይም በእንገሊዘኛው አገላለጽ *Moral Autonomy and Inistitutional autonomy* በመባልም ይታወቀል፡፡ ጠለቅ ላለ ማብራሪያ Yared Legesse M. (Dr.), "Court-Stripping: A Threat to Judicial independence", in Gedion Thimothewos and Helen Fikre (Eds), The FDRE Constitution: Some perspectives on the institutional dimension, *Ethiopian Constituional Law Series,* Vol. VI, College of Law and Goverance, School of Law, AAU, p. 104 ይመልከቱ

independence) ናቸው። ውሳኔያዊ ነፃነት ሲባል ዳኞች የዳኝነት ሥራቸውን ሲያከናውኑ ያላቸውን ነፃነት የሚመለከት ነው።

> Decisional independence means that in the making of judicial decisions and exercising other official duties, individual judges are subject to no other authority but the law.
>
> ውሳኔያዊ ነፃነት ማለት ዳኞች የዳኝነትም ሆነ ሌሎች በሕግ የተሰጣቸውን ሥልጣናቸውን በአግባቡ ሥራ ላይ በሚያውሉበት ወቅት ከማንኛውም አካል ተጽእኖና ቁጥጥር ነፃ ናቸው ማለት ነው።[9] (ትርጉም የጸሐፊው)

ዳኛ በአንድ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ከተከራካሪ ወገኖች በኩል ከሚቀርብ ክርክር፣ ከፍሬነገር ከማስረጃና ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ሕግ በስተቀር ሌሎች ነገሮች ተጽዕኖ ሊያሳድሩበት አይገባም። በዚሁ መሠረት ውሳኔያዊ ነፃነት፣ በውሳኔ አሰጣጥም ሆነ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ከማንኛውም የመንግሥት አካል፣ ባለሥልጣንና ግለሰብ አላግባብ ጣልቃ ገብነት፣ ተጽዕኖና ግፊት ነፃ መሆንን የሚጠይቅ ነው። ዳኛ የቀረበለትን ጉዳይ ሲወስን ከእነዚህ አካላት ትዕዛዝ ወይም መመሪያ መቀበል የለበትም። በተጨማሪም ውሳኔያዊ ነፃነት ከዳኛው የግል ፍላጎት ስሜትና አድሎ ነፃ መሆንን የሚጠይቅ ነው። ዳኛ በሚቀርብለት ጉዳይ ላይ ምንም ፍላጎት የሌለው (disinterested party) ገለልተኛ ውሳኔ ሰጪ መሆን አለበት። ሕዝቡ በዳኞችና በፍርድ ቤቶች ላይ እምነት እንዲኖረው ዳኛ በሚወስነው ጉዳይና በፍርድ ሂደቱ ላይ ግልጽ የሆነ ገለልተኝናትና ነፃነት (apparent independence) ሊኖረው ይገባል። ዳኛ ገለልተኛነቱን ጥያቄ ውስጥ ሊያስገቡ ከሚችሉ ተግባራት ሁሉ መቆጠብ ወይም ራሱን ማግለል ይጠበቅበታል።

የውሳኔያዊ ነፃነት አስፈላጊነት የበለጠ የሚጎላው ከተከራካሪ ወገኖች ውስጥ አንዱ የመንግሥት አካል ወይም ጉዳዩ የመንግሥትን ጥቅም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚነካ ወይም ከፖለቲካ ጋር ተያያዥነት ያለው ሲሆን ነው። ዳኛ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ሕጉን ብቻ መሠረት በማድረግ ከመንግሥት ጥቅምና ፍላጎት ነፃ ሆኖ፣ የፍርድ ቤቱን ተቋማዊ ነፃነትና የራሱን የዳኛውን ግላዊ ነፃነት እንዲሁም ገለልተኝነት የሚጠብቅና የሚያስጠብቅ መሆን አለበት። ዳኛ የእኩልነት መርህን ተግባራዊ በማድረግ በዳኝነት ሥራ ሂደት ውስጥ የሕግ የበላይነትን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት። ይህ ማንኛውም ዳኛ ሊመራበትና ሊተገበረው የሚገባው መርህ ነው። ግላዊ ነፃነትን ስንመለከት ደግሞ ከዳኞች የሥራ ዘመን ዋስትና፣ ምልመላ፣ ሹመት፣ ዕድገት፣ ዝውውር፣ የዲሲፕሊን እርምጃ፣ ከሥራ ማሰናበትና ከክፍያ ጋር የተያያዘ ነው።

የዳኞችን የሥራ ዘመን ከሕግ አስፈጻሚው ወይም ከሕግ አውጪው ፍላጎት ላይ እንዲመሠረት ማድረግ ከዳኝነት ነፃነት መርህ ጋር የሚጋጭ ነው። ዳኛ የቀረበለትን ጉዳይ በፍሬ ነገር፣ ማስረጃና አግባብነት ካለው ሕግ ላይ ብቻ ተመሥርቶ እንዲወስን ሁኔታዎች መመቻቸት አለባቸው። ከዚህ ውስጥ የዳኞች ግላዊ ነፃነት ዋስትና እንዲኖረው ማድረግ አንዱ ነው። እንደ አንድ ምሁር አገላለጽ፣ "ግላዊ ነፃነት የዳኞች

---

9 ዝኒ ከማሁ

የሥራ ዘመን ከሌሎች የመንግሥት አካላት አላግባብ ተጽእኖና ከፖለቲካ አካላት ቁጥጥር ነፃ እንዲሆን የሚጠይቅ ነው፡፡"[10] (ትርጉም የጸሐፊው)

### 1.2 ተቋማዊ ነፃነት

የመንግሥትን ሥልጣን በሦስት ማለትም ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚና ሕግ ተርጓሚ ብሎ መከፋፈል የተለመደ ነው፡፡ ከሦስቱ ዋና ዋና የመንግሥት አካላት ውስጥ አንደኛውን ዘርፍ የሚይዙት ፍርድ ቤቶች ሕግ የመተርጎም ሥልጣን የተሰጣቸው ናቸው፡፡ የፍርድ ቤቶች ተቋማዊ ነፃነትም ከዚሁ የመንግሥት ሥልጣን ክፍፍል ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አንድ ምሁር ተቋማዊ ነፃነትን እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡

> Institutional independence of the judiciary means that the judiciary is not subject to pressure from either the executive or legislature and is not subordinate to either of them particularly in the area of administration of courts.
>
> የፍርድ ቤቶች ተቋማዊ ነፃነት ሲባል የዳኝነት አካላት ከሕግ አስፈጻሚውም ሆነ ከሕግ አውጪው መዋቅራዊ ተጽዕኖ ነፃ መሆናቸውን፣ እንዲሁም ራሳቸውን በራሳቸው በማስተዳደር ረገድ ከሁለቱም አካላት ሥር አለመሆናቸውን የሚያስገነዝብ ነው፡፡[11] (ትርጉም የጸሐፊው)

ከዚህ አገላለጽ እንደምንረዳው ተቋማዊ ነፃነት ፍርድ ቤትን እንደ ሦስተኛ የመንግሥት አካል መቋቋምና መኖር ብቻ የሚመለከት ሳይሆን ከሕግ አውጪና ክሕግ አስፈጻሚው ተጽዕኖ በተለይም ፍርድ ቤትን ማስተዳደር በተመለከተ ነፃ መሆን የሚጠይቅ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ተቋማዊ ነፃነት ፍርድ ቤት እንደ ተቋም ከሕግ አውጪውና ከሕግ አስፈፃሚው አካል ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ የራሱን የውስጥ ጉዳይ ለመወሰን ያለውን ነፃነት የሚመለከት ነው፡፡

የፍርድ ቤት የማስተዳደር ነፃነትም ሁለት ዐበይት ክፍሎች አሉት፡፡ እነሱም ዳኞችንና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን የማስተዳደር ነፃነትና የፋይናንስ ወይም የበጀት ነፃነት ናቸው፡፡ ዳኞችን የማስተዳደር ነፃነት የዳኞች ምልመላ፣ ሹመት፣ ዝውውር፣ ዕድገት፣ ዲሲፕሊን፣ ከሥራ ማሰናበት፣ ደሞዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ይመከለታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን መቅጠርና ማሰናበት ደሞዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞቻቸውን በተመለከተ ፍርድ ቤት እንደ ተቋም ሊኖረው የሚችለውን ነፃነት የሚመለከት ነው፡፡

የፋይናንስ ወይም በጀት አስተዳደር ነፃነት ፍርድ ቤቶች የሚያስፈልጋቸውን በጀት መጠን አዘጋጅተው ለሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ ማቅረብና በጀቱም ከጸደቀ በኋላ ከሥራ አስፈጻሚው አካል ጣልቃ ገብነት ውጪ በጀቱን የማስተዳደር ነፃነትን የሚያጠቃልል ነው፡፡ ነገር ግን ከፍርድ ቤቶች የተቋማዊ ነፃነት ጋር ተያይዞ አሁንም

---

[10] ዝኒ ከማሁ

"By personal independence of judges is to mean the enjoyment by individual judges of judicial terms of office and tenure free from the undue or improper influence and control of the political branches".

[11] ዝኒ ከማሁ

ድረስ ሀገራት አንድ ዓይነት አካሄድ አይከተሉም፡፡ ፍርድ ቤቶችን ማን ያስተዳድር የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ ለመመለስ ወይም ፍርድ ቤቶችን የማስተዳደር ኃላፊነትን በተመለከተ የተለያዩ ሞዴሎች አሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ መሠረታዊ የተባሉትን አራት ሞዴሎች እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡[12]

አንደኛው *የፍርድ ቤቶች ራስን በራስ የማስተዳደር ብቸኛ ሥልጣን ሞዴል* (the exclusive judicial responsibility model) የሚባለው ነው፡፡ በዚህ ሞዴል ፍርድ ቤትን የማስተዳደር ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ ለራሱ ለፍርድ ቤት የተተወ ነው፡፡ ይህ ሞዴል ሁለት ንዑስ ሞዴሎች አሉት፡፡ አንደኛው ግለሰባዊ ንዑስ ሞዴል (Individual sub-model) ተብሎ የሚጠራ ሲሆን በዚህ ንዑስ ሞዴል መሠረት ፍርድ ቤትን የማስተዳደር ኃላፊነት ለአንድ ዳኛ የተተወ ነው፡፡ ለምሳሌ በአሜሪካ የኒውዮርክ ክፍለ ግዛት ይህንን አካሄድ ትከተላለች፡፡[13] ሁለተኛው የጋራ ወይም የቡድን ንዑስ ሞዴል (collective sub-model) ተብሎ የሚጠራው ሲሆን በዚህ ንዑስ ሞዴል ፍርድ ቤትን የማስተዳደር ኃላፊነት ከፍርድ ቤት ተውጣጥቶ ለተቋቋመ አካል የሚሰጥ ነው፡፡ ለምሳሌ የአሜሪካ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትንና ፓርቱጋልን መጥቀስ ይቻላል፡፡[14]

ሁለተኛው *አስፈጻሚው አካል ፍርድ ቤቶችን የማስተዳደር ብቸኛ ሥልጣን ሞዴል* (the exclusive executive responsibility model) የሚባለው ነው፡፡ ይህ ሞዴል የመጀመሪያው (*ማለትም የፍርድ ቤቶች ራስን በራስ የማስተዳደር ብቸኛ ሥልጣን ሞዴል/* the exclusive judicial responsibility model*) ተቃራኒ* ነው፡፡ በዚህ በሁለተኛው ሞዴል መሠረት ፍርድ ቤትን የማስተዳደር ኃላፊነት የሕግ አስፈጻሚው አካል ድርሻ ነው፡፡ ለምሳሌ ኖርዌይ፣ ኦስትሪያና ፈረንሳይ ይህንን ሥርዓት ይከተላሉ፡፡[15] በእርግጥ ይህ አካሄድ ከአጠቃላይ ከፍርድ ቤቶች ነፃነት ጋር የሚጣረስ ይመስላል፡፡

ሦስተኛው ሞዴል *የፍርድ ቤቶች በጋራ የማስተዳደር ሥልጣን ሞዴል* (shared executive-judicial model) የሚባለው ነው፡፡ በዚህ ሞዴል መሠረት ፍርድ ቤትን የማስተዳደር ኃላፊነት በሕግ አስፈፃሚውና በፍርድ ቤት የተከፋፈለ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በጀርመንና ካናዳ የላይኛዎቹን ፍርድ ቤቶች የማስተዳደር ኃላፊነት የፍርድ ቤቶች ሲሆን፣ የታችኞቹን ፍርድ ቤቶች የማስተዳደር ኃላፊነት ደግሞ የሕግ አስፈጻሚው ሥልጣን ነው፡፡[16]

አራተኛው ሞዴል *በዘርፈ ብዙ ተቋማት ፍ/ቤቶችን የማስተዳደር ሥልጣን ሞዴል* (multi-branch responsibility model) የሚባለው ሲሆን በዚህ ሞዴል መሠረት ፍርድ ቤትን የማስተዳደር ኃላፊነት ከፍርድ ቤትና ከሌሎቹም ማለትም ከሕግ አውጪ ሕግ አስፈጻሚና እንዲሁም ከሌላ አካል (ለምሳሌ፡- ከጠበቆች ማህበር ወይም ከሌሎች

---

12 ዝኒ ከማሁ

13 Harvey S. (Ed.), (2002). *Developing a court leadership and management curriculum*, the judicial education reference, information and technical transfer project, (unpublished), p. 55

14 ዝኒ ከማሁ በተጨማሪም Maan, B., (2009). *Past and Future of management of courts*, International journal of Court Administration, p. 7 ይመልከቱ፡፡

15 ዝኒ ከማሁ

16 ዝኒ ከማሁ

ኅብረተሰብ ክፍል የተወከሉ ሰዎች) ለተውጣጣ አካል የተሰጠ ነው፡፡ ይህ አካል ቦርድ፣ ኮሚሽን፣ ኮንፈረንስ፣ ዳኞች ጉባኤ ተብሎ በተለያየ ስም ይጠራል፡፡ ለምሳሌ፡- ሀገራችን ኢትዮጵያን፣ ከላቲን አሜሪካ ሀገሮች አርጀቲናና ብራዚልን፣ ከምዕራብ አውሮፓ ደግሞ ስፔንና ጣልያንን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በምዕራብ አውሮፓ ሀገሮች የዳኞች ጉባኤ ሕግ አስፈጻሚው በፍርድ ቤቶች ላይ ያለውን ሥልጣን ለመገደብ የተቋቋመ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት የዳኞችን ሹመትና እድገት ከሕግ አስፈጻሚው ሥልጣን ውጪ በማድረግ ራሱን ለቻለ ተቋም እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ ሀገሮች በራሳቸው ልዩ ሁኔታ፣ የሕግ ሥርዓትና ታሪክ ላይ በመመሥረት ከላይ የተጠቀሱትን አንዱን ወይም በማጣመር ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ያላቸው ሞዴሎችን ሊመርጡ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ግን የሞዴሎቹ ምርጫ ፍርድ ቤቶች ሊኖራቸው በሚችለው ነፃነት ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል፡፡

የዳኝነት ተቋማዊ ነፃነትን ለመጠበቅ ሌሎች ሊተገበሩ የሚገባቸው መሠረታዊ መርሆች አሉ፡፡[17] ከእነዚህ ውስጥ ከመደበኛ ፍርድ ቤት ውጭ ጊዜያዊ ፍርድ ቤቶች ማቋቋምን የሚከለክል መርህ (the principle against ad hoc courts) እና ድህረ-ውሳኔ የዳኝነት ነፃነት መርህ (the principle of post-decisional independence) ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡፡ ድህረ-ውሳኔ የዳኝነት ነፃነት መርህ በሦስቱም የመንግሥት አካላት የሥልጣን ክፍፍል መሠረት የሕግ አስፈጻሚ አካል የፍርድ ቤት ውሳኔን በመፈጸምና በማስፈጸም ረገድ ያለበትን የሚመለከት ነው፡፡ ይህም በፍርድ አፈጻጸም ሂደት አስፈፃሚው አካል ምንም ዓይነት መሰናክል እንዳይፈጠር ግዴታ የሚጥል መርህ ነው፡፡ ለማጠቃለል፣ የራሳቸውን የሰው ኃይል ካለማንም ጣልቃ ገብነት ማስተዳደራቸው፣ እንዲሁም በጀታቸውን ካለማንም ጣልቃ ገብነት (ም/ቤትን ብቻ በማስፈቀድ) የሚያስተዳድሩና በበጀታቸው ላይ የሚያዙ መሆናቸው የፍርድ ቤቶች ዋነኛ ተቋማዊ ነፃነት መገለጫዎች ከሚባሉት ውስጥ የሚገኙ ሥርዓቶች ናቸው፡፡

## 2. ዓለምአቀፍ መለኪያዎችና ተሞክሮዎች

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የዳኝነት ነፃነት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ተቀባይነትና ትኩረት ያገኘ መርህ ነው፡፡ አስፈላጊነቱን በሚመለከት ዓለም አቀፍ መግባባት (global consensus) ያለ ስለመሆኑ የተለያዩ ዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊና ብሔራዊ የሕግ ሰነዶችን ማየቱ በቂ ነው፡፡ በሌላ በኩል ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በሀገሮች መካከል ካለው የፖለቲካ፣ የሕግና የኢኮኖሚ ልዩነቶች አኳያ የመርሁ ይዘት፣ ስልትና ተግባራዊ አፈፃፀም ደረጃ ይለያያል፡፡ ያም ሆኖ ግን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ይብዛም ይነስ የጋራ መግባባት የተደረሰባቸው የዳኝነት ነፃነት መሥረታዊ መርሆዎች አሉ፡፡ በዚህ ረገድ የተዘጋጀው ረቂቅ (The United Nation's Draft Principles on the Independence of the Judiciary of 1981) በመግቢያው ውስጥ ይህን መሠረታዊ መርህ እንደሚከተለው ይገልፃል፡-

[17] Alemayehu Tegene (2007), *Independence and Accountability of Oromia Regional State Judiciary in light of the Judicial Reform Program*, (Unpublished), LLM Thesis, AAU, Faculty of Law, p. 16

በሀገሮች መካከል የፖለቲካና የሕግ ሥርዓት ልዩነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ስለዳኝነት ነፃነት መርህና ስለ መመዘኛዎች መነሻ ወለል መሠረታዊ የሆነ መግባባት አለ። እነዚህ የዳኝነት ነፃነት መሠረታዊ መርሆችና መመዘኛዎች በሚከተሉት ዓለም አቀፋዊ ይዘት ባላቸው ሰነዶች ውስጥ ተካተው ይገኛሉ።[18]

1. የተባበሩት መንግሥታት የፍርድ ቤት ነፃነት መርሆች ረቂቅ (The United Nations Draft Principles on the Independence of the Judiciary, 1981)
2. የዓለም አቀፍ ጠበቆች ማህበር የዳኝነት ነፃነት መመዘኛዎች መነሻ ወለል (The International Bar Association and Minimum Standard of judicial Independence 1982 /New Delhi Standards)
3. የፍትሕ ነፃነት ሁል-አቀፍ የሞንትሪያል መግለጫ (The Montreal Universal Declaration on the Independence of Justice of 1983 /Universal Declaration)
4. የተባበሩት መንግሥታት የፍርድ ቤት ነፃነት መሠረታዊ መርሆች (The United Nations Basic Principles on the Independence of the Judiciary of 1985)
5. ስለዳኝነት ሥራ አካሄድ በባንጋሎር የወጡ መርሆዎች (The Bangalore Principles of Judicial Conduct of 2002)
6. የፍርድ ቤት ነፃነትና ገለልተኝነት ሁል-አቀፍ መግለጫ ረቂቅ (Draft Universal Declaration on the Independence and Impartiality of the Judiciary of 1989)[19]

---

18 USAID, (2009), *Guide to Court Reform and the role of Court Personel*, (Unpublished), p. 17

"Notwithstanding the diversities of political system and legal mechanism in different countries there is a basic and substantial consensus on the principles and minimum standards relating to the independence of justice in the constitutions and legal systems of world."

19 ከነዚህ በተጨማሪ ሌሎች ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ሰነዶችም ይገኛሉ። እነዚህም 1. Draft Principles on the Independence of the Judiciary ("Siracusa Principles"), prepared by a committee of experts convened by the International Association of Penal Law, the International Commission of Jurists, and the Centre for the Independence of Judges and Lawyers, 1981 (በተለምዶ የሲራኩስ መርሆች ረቂቅ ተብሎ የሚጠራው) ፣ 2. Minimum Standards of Judicial Independence adopted by the International Bar Association, 1982. 3. Draft Universal Declaration on the Independence of Justice ("Singhvi Declaration") United Nations Special Rapporteur on the Study on the Independence of the Judiciary, 1989. 4. The Beijing Statement of Principles of the Independence of the Judiciary in the Lawasia Region, adopted by the 6th Conference of Chief Justices, August 1997. 5. The Latimer House Guidelines for the Commonwealth on good practice governing relations between the Executive, Parliament and the Judiciary in the promotion of good governance, the rule of law and human rights to ensure the effective implementation of the Harare Principles,

የዳኝነት ነፃነት መስፈኑን ለማረጋገጥ የሚረዱ መስፈርቶች በእነዚህ ሰነዶች ውስጥ ተካተው ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ሰነዶች የአስገዳጅነት ባህሪ ባይኖራቸውም የዳኝነት ነፃነትን ለማስፈን ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች ወይም ሀገሮች ሊከተሉ የሚገባቸውን ስልቶች የሚጠቁሙ በመሆናቸው ጠቀሜታቸው የጎላ ነው፡፡ በተጨማሪም የፍርድ ቤቶችን ማሻሻያ ፕሮግራም እየተገበሩ ያሉ ሀገሮች የማሻሻያ ፕሮግራማቸውን ውጤታማነት ለመመዘን እነዚህን መስፈርቶች ይጠቀማሉ፡፡ በእነዚህ ሰነዶች ውስጥ የተካተቱት ዓለም አቀፍ የዳኝነት ነፃነት መመዘኛ ወለሎች (minimum standards) የሥራ ዋስትና፣ በቂ ክፍያና ሕገ መንግሥታዊ ጥበቃ፣ የውሳኔ አሰጣጥና ሂደት ከበላይ አለቆች ጣልቃ ገብነት ነፃ መሆን፣ የፍርድ ቤትን ውሳኔ በማስፈጸም ረገድ የሕግ አስፈጻሚ እገዛ፣ ወደኋላ ተመልሶ የሚሠራ ሕግ አለመኖር፣ ግልጽ የሆነ የሥነ ምግባር ደንብ፣ አስተዳደራዊ ነፃነት፣ ዝውውር፣ ግልጽና ተጨባጭ የእድገት መመዘኛዎች እና ሌሎች ይገኙበታል፡፡ ከነዚህ በርካታ ነጥቦች መካከል አንዱ ለዚህ ጽሁፍ መነሻ የሆነው የተቋማዊ/አስተዳደራዊ ነፃነት መርህና አሠራር ነው፡፡

### *ተቋማዊ ነፃነትን በሚመለከት ዓለምአቀፍ ተሞክሮዎች*

ተቋማዊ ነፃነት ፍርድ ቤት እንደ ተቋም ዳኞችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን እንዲሁም በጀትን በማስተዳደር ረገድ ያለውን ነፃነት በዋነኝነት እንደሚመለከት ቀደም ሲል ተመለክቷል፡፡ በተባበሩት መንግሥታት የዳኝነት ነፃነት መርሆዎች እንደተገለፀው፣ ፍርድ ቤትን የማስተዳደር ዋናው ኃላፊነት ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ጨምሮ ለፍርድ ቤት ወይም ከፍርድ ቤትና ከሌሎች አካላት ለተውጣጣ አካል መሰጠት አለበት፡፡[20] በዚህ አካል ውስጥ ከፍርድ ቤት የሚወከሉ ሰዎች አብላጫውን ቁጥር መያዝ አለባቸው፡፡ ይህም ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው *የዘርፈ ብዙ ተቋማት ሥልጣን ሞዴል* (multi-branch responsibility model) የተሰኘው አካሄድ ከሀገራት አልፎ ዓለምአቀፍ ዕውቅና ያገኘ ስልት መሆኑን ያሳይል፡፡ በዚህ መመዘኛ መሠረት የዳኞች ምልመላ፣ ሹመት፣ ዝውውር፣ እድገት፣ ዲሲፕሊን፣ ከሥራ ማሰናበት እንዲሁም ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን መቅጠርና ከሥራ ማሰናት ከሕግ አስፈጻሚው አካል ቁጥጥር የራቀ መሆን አለበት፡፡

በሌላ በኩል የቆየ የዲሞክራሲ ታሪክና ልምድ ባላቸው ሀገሮች የዳኞች ሹመትና እድገት ከፍርድ ቤት ውጪ በሆነ አካል እንዲከናወን መደረጉ ከዳኝነት ነፃነት መርህ ጋር ያለው ተዛምዶ በዓለም አቀፍ ጠበቆች ማህበር የዳኝነት ነፃነት መመዘኛ ወለሎች (minimum standards) ውስጥ ተመልክቷል፡፡ ይህ ማለት ግን የዲሞክራሲ ባህል ባልዳበረባቸው ሀገሮች ሌሎች የመንግሥት አካላት በፍትህ አስተዳደር ውስጥ አይሳተፉም ማለት አይደለም፡፡ በፍትሕ አስተዳደር ውስጥ የመንግሥት አካላትን ተሳትፎ ማስቀረት አይቻልም፡፡ ሆኖም ግን የዳኝነት ነፃነትን ለመጠበቅ የፍርድ ቤትን የውስጥ ጉዳይ በተመለከተ የሕግ አስፈጻሚው ወይም የሕግ አውጪው አካል ተሳትፎ የመንግሥት ሥርዓቱ የግድ በሚላቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ የተገደበ መሆን አለበት

1998. (*Commentary on The Banglore Principles of Judicial Conduct,* UN Office of Drug and Crime, September 2002, p. 12 ይመለከቷል)

[20] International Commission of Jurists (2007). *International Principles on the Independence and Accountability of Judges, Lawyers and Prosecutors* (Practioners Guide No. 1), Geneva, Switherland*,* p. 21

ተብሎ ይታመናል፡፡[21] ለዚህም የዳኞችን ሹመትና ከሥራ ማሰናበት እንዲሁም በጀትን ማጽደቅ እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡

የፍርድ ቤቶች ተቋማዊ/አስተዳደራዊ ነፃነት ዋነኛው መገለጫ የበጀትና የፍርድ ቤቶች የድጋፍ ሰጪ ሰው ኃይል አስተዳደር ነፃነት ነው፡፡ በተለይም የበጀት አስተዳደር ነፃነት ለፍርድ ቤቶች ተቋማዊ ነፃነት ወሳኝ እንደሆነ የበርካታ ሀገራት ልምድና የዓለም አቀፍ የዳኝነት ነፃነት መርህ ሰነዶች ይገልፃሉ፡፡ የዓለም አቀፍ የዳኝነት ነፃነት መመዘኛ ወለል እንደሚያሳየው ፍርድ ቤቶች በፍትሕ አስተዳደር ውስጥ የሚጠበቅባቸውን ሚና ይጫወቱ ዘንድ በቂ በጀት ሊመደብላቸው ይገባል፡፡ የፍርድ ቤቶች በጀት አግባብነት ካለው አካል ጋር በመቀናጀት የሚዘጋጅ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ፍርድ ቤቶች ተገቢውን ተሳትፎ ማድረግና በጀትም ሲፈቀድ የማስተዳደር ሥልጣን ሊኖራቸው ይገባል፡፡

የበጀት ነፃነትን በተመለከተ የሀገሮች ልምድ የተለያየ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ አሜሪካ፣ ህንድ፣ ጃፓንና ፊንላንድን ብንወስድ ፍርድ ቤቶች የራሳቸውን በጀት ግምት አዘጋጅተው ለሕግ አውጪው በቀጥታ ያቀርባሉ፡፡ ሲፈቀድም የተፈቀደላቸውን በጀት ካለ አስፈጻሚ አካል ጣልቃ ገብነት የማስተዳደር ነፃነት አላቸው፡፡ በአሜሪካን የፍርድ ቤቱን በጀት ያለአስፈጻሚ አካል ጣልቃ ገብነት አዘጋጅቶ ማቅረብ የተቋማዊ ነፃነት መሠረታዊ ገጽታና ሕገ መንግሥቱ ካስቀመጠው የሥልጣን ክፍፍል የሚመነጭ ነው፡፡ አንድ አሜሪካዊ ዳኛ እንደገለፁት የአስፈፃሚ አካል የፍርድ ቤቶችን በጀት እንዲያዘጋጅ ማድረግ በሕገ መንግሥቱ ከተደነገገው የመንግሥት አካላት የሥልጣን ክፍፍል ጋር የሚጋጭ ነው፡፡[22]

የጀርመን፣ ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ፣ ኔዘርላንድስ፣ ብራዚል፣ ደቡብ አፍሪካና የካናዳ ልምድ ከአሜሪካ፣ ህንድ ጃፓንና ፊንላንድ ተቃራኒ ነው፡፡ በእነዚህ ሀገሮች ፍርድ ቤቶች የራሳቸውን በጀት ቀጥታ ለሕግ አውጪው አካል አቅርበው የማስጸደቅ ሥልጣን የላቸውም፡፡ የፍርድ ቤቶች በጀት ለሕግ አውጪው የሚቀርበው በሕግ አስፈጻሚው በኩል ነው፡፡ በእነዚህ ሀገሮች የጸደቀውን በጀት በማስተዳደር በኩልም አስፈጻሚው አካል ከፍተኛ ሚና አለው፡፡[23]

ሀገራት የፍርድ ቤቶች የበጀት ነፃነትን ለማስከበር በርካታ ፈተናዎች ገጥሟቿል፡፡ በተለይም የአስፈጻሚው ፖለቲካዊ ክንፍ ለዳኝነት አካሉ በጀት በመመደቡና በመፍቀዱ ሂደት ላይ ለፍርድ ቤቶች ያለው አመለካከትና ግንኙነት ይወስነዋል፡፡ ለምሳሌ በፖላንድ፣ ስሎቬኪያ፣ ቡልጋሪያ፣ ዩክሬንና ሩሲያ ፌዴሬሽን ፍርድ ቤቶች በቂ በጀት አይመደብላቸውም ብቻ ሳይሆን በየጊዜው እያሽቆለቆለ በሚሄድ የበጀት አመዳደብ ምክንያት ፍርድ ቤቶቹ ከሚሰበስቡት የዳኝነት ክፍያ (court fee) ወጪያቸውን ለመሸፈን ተገደዋል፤ ግላዊ የገንዘብ ምንጮች እስከ ማማተር ድረስ የተደረሰበትም

[21] Rekosh, Edwin, (2002). *Emrging lessons from reform efforts in Eastern Europe and Eurasia*, p. 53 and p. 72 in Office of Democracy and Governance, *Giudance for promoting Judicial Independence and Impartiality*, Technical publication series, Washington, USA

[22] "… It is in conflict with the division of power which the constitution contemplates to allow the executive department to formulate the budget for the judiciary".
Sarviilina, S., (2010), *Court Administration in Finland*, Stocholm Institute for Scandinevian Law, (unpublished), p. 596

[23] Rekosh, Edwin, *supra* note 21., p. 74

ዘመን ነበር። በቡልጋሪያ የዳኝነት አስተዳደር ጉባኤው በጀት በማዘጋጀትና በመቆጣጠር ረገድ ሥልጣን ያለው ቢሆንም በጀቱ በፓርላማው እንዲጸድቅ የሚላከው በካቢኔው (በሚኒስትሮች ምክር ቤት) በኩል ነው። በፍርድ ቤት በጀት ላይ የቡልጋሪያ ፍትሕ ሚኒስቴር ወሳኝ ሚና ያለው ሲሆን፣ የራሱን የበጀት ስሌት የማቅረብና በፍ/ቤቱ የዳኝነት አስተዳደር ጉባኤ የቀረበውንም የበጀት ረቂቅ የመቃወም ሥልጣን አለው።

በፖላንድም የሥር ፍ/ቤቶች፣ የጠቅላይ ፍ/ቤቱንና የጠቅላይ አስተዳደር ፍ/ቤቱን በጀት በአብዛኛው የሚቆጣጠረው የሀገሪቱ ፍትሕ ሚኒስቴር ነው። በአንፃሩ በጂኦርጂያ ያለው አሠራር የፍ/ቤቶችን ነፃነት ከሌሎቹ የምሥራቅ አውሮፓ ሀገራት በተሻለ የሚያስጠብቅ ይመስላል።[24] የበጀት አስተዳደሩ ሙሉ በሙሉ በፍ/ቤቱ ቁጥጥር ሥር ያለ ሲሆን በፍ/ቤቱ አደረጃጀት ውስጥ የሚገኘው የሎጂስቲክስ የሥራ ክፍል ከጠቅላይ ፍ/ቤቱ ፕሬዚደንት በሚሰጠው መመሪያና አቅጣጫ መሠረት የበጀት ረቂቁን ያዘጋጃል፤ ይህ ረቂቅ በፕሬዚደንቱ በኩል ለፍትህ አስተዳደር ጉባኤው (Council of Justice) ቀርቦ ከጸደቀ በኋላ ለመጨረሻው ማጽደቅ በጠቅላይ ፍ/ቤቱ ፕሬዚደንት በኩል ለፓርላማው ይቀርባል።[25]

በአፍሪካም ያለው ቀደም ብለን ካየነው ከምሥራቅ አውሮፓና ዩሬሺያ ልምድ ብዙም አይለይም። ለምሳሌ ኮመን ሎው የሕግ ሥርዓት የሚከተሉና እንግሊዘኛ ተናጋሪ የሆኑ ሀገራት (ኬኒያ፣ ናይጄሪያ፣ ኡጋንዳ፣ ዛምቢያ፣ ዚምባብዌ፣ ቦትሷናና ታንዛኒያ) ላይ በተሠራ አንድ ጥናት በነዚህ ሀገራት ፍርድ ቤቶች በበጀት አመዳደብ ላይ ያን ያህል ትኩረት እንደማያገኙና ዘወትር በበጀት እጥረት እንደሚያማርሩ ተገልጧል።[26] ይህንን የበጀት ችግር ለመቅረፍና የፍርድ ቤቶችን የበጀት ነፃነት ለማስጠበቅ እነዚህ ሀገራት እንደመፍትሔ የወሰዱት አማራጭ በሕግ አውጪው በኩል ለፍርድ ቤቶች ጥቅል በጀት (consolidated fund) እንዲመደብ ማድረግ ነው። ለምሳሌ በአፍሪካ ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎች ሀገራት ፍርድ ቤቶች ለሀገሪቱ ከሚመደበው ጥቅል በጀት ውስጥ በመቶኛ ድርሻ እንዲኖራቸው ተደርጎ ይህም በጀት ያለማንም ጣልቃ ገብነት በዳኝነት ጉባዔው እንዲተዳደር የሚደረግበትን ሥርዓት ዘርግተዋል።[27]

በሀገረ ህንድ ደግሞ ያለው አሠራር ከዚህም ጠንከር ይላል። የህንድ ፍርድ ቤቶች በጀትም ሆነ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ደመወዝ፣ ጥቅማጥቅምና ሌሎች አስተዳደራዊ ወጪዎች የሚሸፈኑት ለሀገሪቱ ከተመደበውና የሕግ አውጭው ም/ቤትም ቢሆን ሊያሻሽለው ወይም ሊለውጠው ከማይችለው የፍርድ ቤት ድርሻ ከሆነው ጥቅል በጀት ነው።[28] በህንድ ከበጀት አስተዳደሩ በተጨማሪ የድጋፍ ሰጪው የሰው ኃይል አስተዳደር ሙሉ በሙሉ በፍርድ ቤቱ ቁጥጥር ሥር ነው።[29]

---

[24] ዝኒ ከማሁ ገጽ 63- 65

[25] ዝኒ ከማሁ

[26] Widner, Jennifer, (January 2002). "Judicial Independence in Common Law Africa", in Office of Democracy and Governance, *Giudance for promoting Judicial Independence and Impartiality*, Technical publication series, Washington, USA, **ገጽ** 48

[27] ለምሳሌ የዩጋንዳን 2006 (እ.ኤ.አ) ሕገ መንግሥት አንቀጽ 128 (5) እና የኬኒያን 2010 (እ.ኤ.አ) ሕገ መንግሥት አንቀጽ 173 መመልከት ይቻላል።

[28] M.P. Singh (2000). *Securing the Independence of the Judiciary-The Indian Experience*, Indian International & Comparative Law Review, Vol 10 No. 2, **ገጽ** 253

[29] ዝኒ ከማሁ

የበጀትና የድጋፍ ሰጪው የሰው ኃይልን በተመለከተ በደቡብ አሜሪካ ያለውን አተገባበር ስንመለከት፣ ቀደም ብለን ካየናቸው በተለይም ከምሥራቅ አውሮፓ ሀገራት የተሻለ የዳኝነት ተቋማዊ/አስተዳደራዊ ነፃነት ያለባቸው ሀገራት እንደሚገኙ ማወቅ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ በኮስታሪካና በኤልሳልቫዶር ፍ/ቤቶች ከሀገሪቱ ጥቅል በጀት ውስጥ የስድስት (6) በመቶ ድርሻ ያላቸው ሲሆን በጉዋቲማላና በፓናማ ደግሞ የሁለት (2) በመቶ ድርሻ እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡[30] በቦሊቪያ፣ በፓራጓይና በቺሊም በተመሳሳይ ሁኔታ ፍ/ቤቶች በሚመደብላቸው ጥቅል በጀት ዳኞችን ብቻ ሳይሆን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞቻቸውንም ከአስፈጻሚው አካል እጅና ጣልቃ ገብነት ነፃ በሆነ መልኩ ያስተዳድራሉ፡፡[31]

## 3. የዳኝነት (ፍርድ ቤት) ታሪካዊ ዳራና አመሠራረት በኢትዮጵያ

ፍ/ቤቶች የተቋቋሙት ለሚነሱ ማናኛውም ክርክሮች እንዲሁም በሥርዓቱ ላይ ለሚደርሰው ችግር በሥልጣናቸው ሥር ተገቢ ውሳኔ (ፍርድ) ለመስጠት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪና ከዚህም ጋር ተያይዞ የኀብረተሰቡ አባላት መብታቸውና ግዴታቸው እንዲከበር፤ ግንኙነታቸው ሳይናጋ ተከባብረው እንዲኖሩ፤ የአገሪቱ ሰላምና ደህንነት ተጠብቆና ተረጋግቶ እንዲቀጥል፤ የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ እና ዲሞክራሲ እንዲሰፍን ፍርድ ቤቶች ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ በኢትዮጵያ መደበኛ ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ከመቋቋማቸው በፊትና የተፃፈ ሕገ መንግሥት ባልነበረበት ዘመን (ቅድመ 1923) ሕዝቡ ይዳኝ የነበረው ባህሉን፣ ወጉን እና እምነቱን መሠረት አድርጎ በሚመረጡ ዳኞች እንደነበረ ከታሪክ እንረዳለን፡፡[32] በ15ኛው ክፍለ ዘመን የዳኝነት ሥርዓቱ በተለይ በዘመነ ፍትሐ ነገሥት በሕግ መሠረት እንዲሠራ ጥረት የተደረገ ቢሆንም ያስመዘገበው ውጤት አመርቂ አልነበረም፡፡ ከዚህ በኂላ በተለይም ከአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥትና ከ1923 የመጀመሪያው የተጻፈ ሕገ መንግሥት ጀምሮ የተለያዩና ዘመናዊ የሆኑ ከዳኝነት ጋር የተያያዙ ሕጐች ወጥተዋል፡፡ በዚህም መሠረት፡-

---

[30] Margaret Popkin (January 2002). *Efforts to inhance Judicial independence in Latin America: A Comparative perspective*, in Office of Democracy and Governance, *Giudance for promoting Judicial Independence and Impartiality*, Technical publication series, Washington, USA, **ገጽ** 122

[31] *ዝኒ ከማሁ ገጽ* 123

[32] በዚህ ረገድ ጠለቅ ያለና ዝርዝር መረጃ ለማግኘት Aberra Jembere, (2012 G.C).*An Introduction to the Legal History of Ethiopia (1434-1974), Some Aspects of substantive and procedural laws*, Shama Books and Master Printing Press plc, Addis Ababa, Ethiopia ከገጽ 213-235፣ አበራ ጀምበሬ, (የካቲት 1984 ዓ.ም) *ተጠየቅ ሙግት ልማዳዊው የኢትዮጵያ የክርክር ስልት የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት*, መግቂ 15 አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት ከገጽ 219-236 እንዲሁም Muradu Abdo, *Legal History and Tradition*, (Unpublished material) Addis Ababa University, Faculty of Law, p. 256-267 ይመልከቱ

ሀ) በ1934 ዓ.ም የዳኝነት አካሄድን የሚደነግግ አዋጅ ቁጥር 2/34 የወጣ ሲሆን ይህ አዋጅ ስለዳኝነት ሥራ አካሄድና ስለዳኝነት አከፋፈል እንዲሁም ስለ አጥቢያ ዳኝነት የሚደነግጉ ደንቦችን[33] የያዘ ነበር፡፡

ለ) በ1943 ዓ.ም ፍ/ቤቶች ከጠቅላይ ንጉሠ ነገሥት ፍ/ቤት እስከ ወረዳ ወይም ቀበሌ ፍ/ቤት ድረስ የተቋቋሙ መሆኑን የሚደነግግ አዋጅ ቁጥር 155/1943 ወጥቷል፡፡

ሐ) በ1955 ዓ.ም የፍ/ቤቶችን አደረጃጀት ያሻሻለና የዙፋን ችሎት መቋቋምን ያካተተ አዋጅ ቁጥር 195/1955 ወጥቶ ሥራ ላይ ውሏል፡፡[34]

መ) የዳኞችን ምደባ፣ የደመወዝ ደረጃ፣ እንዲሁም ሥነ-ምግባር በሚመለከት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 323/65 እና የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 438/65 ለመጀመሪያ ጊዜ ታውጀው በሥራ ላይ የዋሉት በ1965 ዓ.ም ነው፡፡[35]

የሌሎቹን ዝርዝር ሕጎች ይዘት ትተን የሁለቱን ንጉሣዊ ሕገ መንግሥቶች እንኳን ለመመልከት ብንሞክር፣ ለምሳሌ የ1923 ሕገ መንግሥት ከአንቀጽ 50 እስከ አንቀጽ 54 ድረስ ስለዳኞችና ስለ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት፣ ውሳኔ አሰጣጥና በቀጥታም ባይሆን ስለዳኝነት ነፃነት በዘመኑ ተራማጅ ሊባል በሚችል መልኩ የተደነገጉ ሲሆን፣ በተመሳሳይ መልኩ የ1948 የተሻሻለው ሕገ መንግሥት ከአንቀጽ 108 እስከ አንቀጽ 112 ድረስ ነፃነታቸውን ባጎናጸፈ መልኩ እንደሚደራጁ ተገልጧል፡፡[36]

የንጉሠ ነገሥቱ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት በደርግ መንግሥት ሲተካ ቀደም ብለው የዳኝነቱን አካሄድና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ለማቋቋም የወጡት አዋጆችና ደንቦች ተሽረው እነዚህኑ ጉዳዮች የሚመለከተው አዋጅ ቁጥር 52/68 በ1968 ዓ.ም ታውጇል፡፡ በ1980 ዓ.ም ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ቁ 1/80 መታወጅን ተከትሎ የሪፐብሊኩ ጠቅላይ ፍ/ቤት ራሱን ችሎ እንዲቋቋም፣ እንዲሁም በአገሪቱ የበላይ የሆነ የዳኝነት አካል ሆኖ እንዲደራጅና እንዲቋቋም፣ በመጀመሪያ አዋጅ ቁጥር 9/1980 በመቀጠልም ይህንን አዋጅ ያሻሻለው አዋጅ ቁጥር 24/1981 ወጥተዋል፡፡[37]

በ1980 ሕገ መንግሥት ላይ የሁሉም ፍ/ቤቶች የዳኞች የሥራ ዘመን የብሔራዊ ወይም የአካባቢ ሸንጎዎች የሥራ ዘመን እንዲሆን፣ እንዲሁም በሁሉም ፍ/ቤቶች በሕዝብ የሚመረጡ እማኝ ዳኞች (People's assessors) እንዲኖሩ በሚል ተደንግጎ ይገኛል፡፡[38] በእርግጥ ይህ የኢ.ሕ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት የፍርድ ቤቶችን ነፃነት

---

[33] ሐምሌ 9 ቀን 1923 ዓ.ም የታወጀው የመጀመሪያው ንጉሠ ነገሥታዊ ሕገ መንግሥት፣ አንቀጽ 53

[34] ይህ ሕግ የወጣው የ1923 ሕገመንግሥት ባሻሻለውና በ1948 ዓ.ም በወጣው ሁለተኛው ሕገመንግሥት አንቀጽ 109፣110 እና 111 ነበር፡፡

[35] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 111

[36] ቃለአብ ታደሰ ስጋቱ (2011), *ሕገመንግሥት በኢትዮጵያ፣ ከፍትሐ ነገሥት እስከ ኢ.ፌ.ዲ.ሪ፣ ሜጋ አሳታሚና ማከፋፈያ*፣ ገጽ 113

[37] መስከረም 1 ቀን 1980 ዓ.ም የጸደቀው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 63(3)/ሐ/ የሪፐብሊኩን ጠቅላይ ፍ/ቤት የማቋቋም ሥልጣን የብሔራዊ ሸንጎ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡

[38] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 100-107

በተመለከተ በአንቀጽ 104 ላይ ዳኞችና እማኝ ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት እንደሚያከናውኑና ከሕግ በስተቀር በማንኛውም ሌላ ሥልጣን እንደማይመሩ ቢደነግግም፣ በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን ድንጋጌ ትርጉም ሊያሳጡ የሚችሉ ድንጋጌዎች በሕገ መንግሥቱ ይገኛሉ። በተለይ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 86(1)(መ) እና 101 አስፈጻሚው በተለይም የሪፐብሊኩ ፕሬዝደንት በፍ/ቤቶች ሥራና እንቅስቃሴ ላይ እጁን ሊያስገባ እንደሚችል የሚያሳዩ ናቸው። ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የፍርድ ቤቶች/ዳኞች የሥራ ዘመን በፖለቲካዊ ተቋማት ላይ በተለይም በብሔራዊ ሸንጎው የሥልጣን ዘመን ላይ ጥገኛ መሆኑንን በቀላሉ መረዳት ይችላል።

ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የደርግ መንግሥትን ሲተካ ጊዜያዊ መንግሥት ለማቋቋም የሽግግር መንግሥት ቻርተር ጸደቀ። በቻርተሩ መሠረትም ዳኝነት ባልተማከለ መልኩ ይካሄድ ዘንድ የማዕከላዊ እና የክልል ፍርድ ቤቶች በሚል ራሳቸውን ችለው እንዲደራጁ ተደርጎ ይህንኑ የቻርተሩን መሠረተ ሓሳብ በመያዝ የፍትሕ አስተዳደር ከማንኛውም ዓይነት ተጽእኖ ነፃ እንዲሆን ለማስቻል አዋጅ ቁጥር 23/1984 እና ይህንኑ አዋጅ ያሻሻለው አዋጅ ቁ. 40/1985 (የማዕከላዊ የሽግግር መንግሥት ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ/እንደተሻሻለ) ታውጀው ሥራ ላይ ውለዋል።[39]

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት በ1987 ዓ.ም. በቁጥር 1/87 ሲታወጅ፣ ፍ/ቤቶች ከማንኛውም ተጽዕኖ ነፃ ሆነው በመደራጀት የፍትሕ ሥራ እንደሚያኪያሂዱ ተደንግጓል።[40] ከዚህ በተጨማሪም ፍርድ ቤቶች ከማንኛውም የመንግሥት አካል፣

---

[39] የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር ቁ. 1/1983 ዓ.ም፣ አንቀጽ 9(ረ)፣ (የኢትዮጵያ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉባኤ ነጋሪት ጋዜጣ፣ ሐምሌ 15 ቀን 1983 ዓ.ም 50ኛ ዓመት ቁ. 1

[40] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 78(1) በግልጽ ነፃ የዳኝነት አካል በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል በማለት ይደነግጋል። የእንግሊዘኛው ቅጂም *an Independent Judiciary is established by this Constitution* ይላል። ይህ ሕገመንግሥታዊ ድንጋጌ ከ1981 የኢሕዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 63(3)/ሐ/ እና 100 (1) እንዲሁም ከ1948 የተሸሻለው የንጉሠ ነገሥቱ ሕገ መንግስት አንቀጽ 108 እና109 በተለየና በተሻለ መልኩ የተቀመጠ ድንጋጌ መሆኑ ይታመናል። ምክኒያቱም የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት የዳኝነት አካላት በሌሎች ተቋማት በሚወጡና በሚሻሩ ሕጎች እንዲቋቋም ሳይሆን በራሱ በሕገ መንግሥቱ ማቋቋሙ በተራ የበታች ሕግ እንደፈለገ ማቋቋም ወይም ማፍረስ እንዳይቻል ሕገ መንግሥታዊ ዋስትና ይሰጣል። ከላይ የተጠቀሱት የቀድሞ ሕገ መንግሥቶች ግን ይህንን ወሳኝ ተቋም እንዲያቋቁሙ ለሕግ አውጪ ምክር ቤቶች ሥልጣን የሰጡ ሲሆን ም/ቤቶቹም በየጊዜው የዳኝነቱን አካል በአዋጅ ሲያቋቁሙና ሲያሻሽሉ ቆይተዋል። ይህም ይብዛም ይነስ የዳኝነት ነፃነት ላይ የራሱ ተጽእኖ እንዳለው ግልጽ መሆን አለበት። በእርግጥ ይህ ንዑስ አንቀጽ ሲረቀቅ አንድ የአርቃቂው ኮሚሽን አባል "……ተቋቁሟል" የሚለው አሁን የተቋቋመ ስለሚያስመስለው በየጊዜው በሚደረጉት ምርጫዎች የሚቋቋምበትም ሁኔታ እንዳለ በመግለጽ ልክ እንደቀድሞዎቹ ሕገ መንግሥቶች "…..ይቋቋማል" በሚል እንዲስተካከል አስተያየት አቅርበው ተቋቁሟል የሚለው ቃል የሕግ ቋንቋ ስለሆነና ሕገ መንግሥቱም የሕጎች የበላይና ምንጭ በመሆኑ ከአሁኑ ነጻ የዳኝነት አካል መቋቋሙን መደንገግ አስፈላጊ መሆኑንን መልስ እንደተሰጠበት ከሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን ቃለ ጉባዔ መረዳት ይቻላል። (የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ጉባኤ ቃለ ጉባኤ ቁጥር 27 እና 28 /ህዳር 21-24 1987 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ/ ገጽ 13)። በእርግጥ ህገ መንግሥቱ አንቀጽ 78(1) ላይ ነፃና ገለልተኛ ዳኝነት ማቋቋሙን በይፋ ቢደነግግም ነፃ ዳኝነት እና ገለልተኛ ዳኝነት ሲባል መገለጫዎቹ ምንድናቸው የሚለውን ዝርዝር ምላሽ አይሰጥም።

ከማንኛውም የመንግሥት ባለሥልጣንም ሆነ ከማንኛውም ሌላ ተጽዕኖ ነፃ እንደሆኑ ተገልጧል፡፡[41] ማንም ሰው ከዚህ መረዳት የሚችለው የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት የዳኝነት አካሉን ማቋቋሙ ብቻ ሳይሆን ለነፃነታቸውም ሕገ መንግሥታዊ ከለላና ዋስትና መስጠቱን ነው፡፡ የፍ/ቤቶችም አደረጃጀት የኢትዮጵያን ፌዴራላዊ ሥርዓት ተከትሎ የፌዴራልና የክልል ፍ/ቤቶች በሚል እንዲዋቀሩ ተደርጓል፡፡[42] በዚህ መሠረት ከላይ በጥቅሉ የተቀመጠውን የዳኝነት ነፃነት ድንጋጌ ተከትሎ በተለይም የዳኞችን ግለሰባዊና ውሳኔያዊ ነፃነት ለማስከበር፣ ዳኞች ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት እንደሚያከናውኑ፣ ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ እንደማይመሩና ሌሎች ጥበቃዎችን ተግባር ላይ ለማዋል የፌዴራል የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ወሳኝ ሚና እንዳለው ሕገ መንግሥቱ ይገልፃል፡፡[43] ይህንኑ መሠረት በማድረግ፣ በአዋጅ ቁጥር 24/1988፣ በመቀጠልም አሁን በሥራ ላይ ባለው በአዋጅ ቁጥር 684/2002 መሠረት የፌዴራል የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በማቋቋምና ዝርዝር ሥልጣንና ተግባሩን በማስቀመጥ ሥራውን እንዲሠራ ተደርጓል፡፡

የፍርድ ቤቶችን በተለይም የዳኞችን ነፃነት እውን ለማድረግ የዳኞች ምልመላ፣ ዝውውርና የዲሲፕሊን እርምጃ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ኃላፊነት መሆኑን ደንግጓል፡፡ ጉባኤውም በፌደራል ደረጃ ብቻ ሳይሆን ክልሎች ሕገ መንግሥታቸውን መሠረት በማድረግ የራሳቸውን የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ እንዲያቋቁሙ ተደርጓል፡፡ ከፌዴራልና ከክልል የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጆች መረዳት እንደሚቻለው የጉባኤው አባሎች ቁጥር የተለያየ ነው፡፡ ለምሳሌ፤ የጉባኤ አባላት በፌዴራል ዘጠኝ፣ በትግራይ 17፣ በኦሮሚያ 9፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል 11፣ በጋምቤላ 16፣ በአማራ ክልል 12 ናቸው፡፡

የጉባኤው አባላት ስብጥርም ይለያያል፡፡ በፌዴራል ደረጃ የተቋቋመው ጉባኤ፣ ከፍርድ ቤትና ከፌደራሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ከጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣ ከሕግ ባለሙያዎች ማህበር፣ ከታዋቂ ግለሰቦች የተወከሉ አባላት ያሉትና የሕግ መምህር ያለበት ነው፡፡ በክልል በሚቋቋሙ ጉባኤዎችን በሚመለከት ለምሳሌ በትግራይ ከፍርድ ቤት፣ ከሴቶች ማህበር፣ ከገበሬ ማህበር፣ ከፍትህ ቢሮ፣ ከጠበቆች ማህበር እና ከአስተዳደርና ፍትህ ዘርፍ አባላት ይወከላሉ፡፡ የኦሮሚያ ክልል የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ከፍርድ ቤትና ከምክር ቤት፣ በደቡብ ክልል ደግሞ ከፍርድ ቤትና ከክልል ምክር ቤት የሚወከሉ ናቸው፡፡[44] እነዚህ የፌዴራል ክልል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤያትም የዳኞች ምልመላ፣ ደመወዝ፣ ዲሲፒሊን፣ ዕድገት፣ ዝውውር፣ አበልና ሕክምና የመወሰን ሥልጣን አላቸው፡፡ የፌደራሉን ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አደረጃጀት በተመለከተ የሕግ ጥያቄዎች ያሉ ቢሆንም የዚህ ጽሑፍ ዋነኛ ዓላማ በፌደራል ፍርድ ቤቶችን ተቋማዊ ነፃነት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡

---

ከባህሪውም አንጻር መስጠትም አይጠበቅበትም፡፡ በሌሎች ሀገራት ልምድ እነዚህና ሌሎች ከሕገመንግሥቱ በተሻለ ዘርዝር ከሌሎች ሕግጋት ጋር ሲነጻጸር ደግሞ ጠቅለል ብለው በተዘጋጁ የዳኝነት ፖሊሲ ሰነዶች ውስጥ እንዲካተቱ የሚደረግባቸው አሠራሮች አሉ፡፡

[41] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት፣ አንቀጽ 79 (2)

[42] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 78 (2) እና (3) ይመለከቷል፡፡

[43] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 79 (4) ፣ አንቀጽ 81 (2) እና (4) - (6) ይመለከቷል፡፡

[44] በዚህ ረገድ የየክልሎቹ ህግጋተ መንግስታትና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ መቋቋሚያ አዋጆች መመልከት ይቻላል፡፡

## 4. የሕገ መንግሥቱና የአዋጅ ቁጥር 25/1988 መርሆዎችና በተግባራዊ አፈጻጸም ረገድ የሚታየው ችግር

ፍርድ ቤቶች የሚያስፈልጋቸውን የበጀት መጠን በቀጥታ በሕገ መንግሥቱ መሠረት የፌደራሉ መንግሥት ከፍተኛና የመጨረሻ የሥልጣን አካል ለሆነው የፌደራሉ መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በማቅረብ እንደሚያስጸድቁ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት በግልጽ ይደነግጋል።[45] ከፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 ስያሜ እንደምንረዳው፣ ይህ አዋጅ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣ ሳይሆን፣ አስቀድሞ በሕገ መንግሥቱ የተቋቋመውን ነፃ የዳኝነት ተቋም ዝርዝር ዳኝነታዊና አስተዳደራዊ ሥልጣን የሚመለከት ሕግ ነው።[46]

የአዋጁ ክፍል አምስት አንቀጽ 16 የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤትን ፕሬዚደንት ሥልጣኖች ይገልፃል። ይህ አንቀጽ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚደንት በሕግ መሠረት የፌዴራል ፍ/ቤቶችን ለማስተዳደር ኃላፊ እንደሆነ በጥቅሉ ደንግጎ፣ በዝርዝር ደግሞ በአንቀጹ ንዑስ ቁ. (2) ሥር ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ተ) ድረስ አሥራ አንድ የሚሆኑ አስተዳደራዊ ኃላፊነቶችን ይዘረዝራል። ከነዚህ አስተዳደራዊ ኃላፊነቶች መካከል፣ በፊደል ተራ (ሐ) ላይ የተሰጠው የፌደራል ፍ/ቤቶችን ዕቅድና በጀት በማዘጋጀት ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የማቅረብና ሲጸድቅ ተግባር ላይ የማዋል ሥልጣንና ኃላፊነት ይገኛል። ይህም ማለት በሕገ መንግሥቱና በዚህ አዋጅ ጭምር ማናቸውም አካል በተለይም የአስፈጻሚው አካል በዳኝነት በጀት ሥራ ውስጥ ጣልቃ እንዳይገባ ተደንግጓል ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪም በዚሁ በአንቀጽ 16(2) ፊደል ተራ (ለ) እና ፊደል ተራ (ረ) መሠረት ከሥር ፍ/ቤቶች ፕሬዚደንቶች ጋር በመመካከር ከዳኞች ውጪ ያሉትን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች የመቅጠርና ትምህርትና ሥልጠና የሚካሄድበትን ሁኔታ የማመቻቸት ሥልጣን ተሰጥቶታል። ስለዚህም በዚህ አዋጅ መሠረት ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን መቅጠርና ማስተዳደር እንዲሁም ሌሎች አስተዳደራዊ ሥራዎችን ማከናወን የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ኃላፊነት እንደሆነ ግልጽ ነው።

### 4.1 የፌደራል ፍ/ቤቶች መዋቅራዊ አደረጃጀትና የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች አስተዳደር

በሦስቱም ፌደራል ፍርድ ቤቶች የሚገኘው የሰው ኃይል በሁለት ታላላቅ ምድቦች (categories) የተከፈለ ሲሆን፣ የመጀመሪያው አስፈጻሚ/ዋናው የሰው ኃይል ምድብ (core/main staff wing) ተብሎ የሚጠራው ነው። ይህም የየፍርድ ቤቶቹን ዳኞች፣ ሬጅስትራሮችና ም/ሬጅስትራሮችን የሚመለከት ሲሆን፣ ምልመላቸው፣ ደመወዛቸው፣ ዝውውራቸው፣ እድገታቸው፣ የዲሲፕሊን ጉዳዮቻቸው፣ ሥልጠናቸው፣ የሥራ

45 የኢ.ፌ.ዴ. ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 79 (6) ይመለከቷል።

46 በርካታ አካላትና የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት አዋጁን የፌደራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ በማለት ሲጠሩት ይሰማል። ነገር ግን ይህ ስህተት እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። ምክኒያቱም አዋጁ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 (Federal Courts Proclamation No. 25/1996) እንጂ የፌደራል ፍርድ ቤቶች *ማቋቋሚያ* አዋጅ (Federal Courts Establishment Proclamation) አይደለም። ምክንያቱም ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግሥቱ የተቋቋሙ በመሆናቸው ሌላ ማቋቋሚያ አዋጅ ማውጣት አስፈላጊም ሕገ መንግሥታዊም ስላልሆነ ነው።

አፈጻጸማቸው፣ ጥቅማ-ጥቅሞቻቸውና ሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮቻቸው የሚከናወኑት በፌደራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 684/2002 መሠረት ነው፡፡

ሁለተኛው የሰው ኃይል ምድብ የድጋፍ ሰጪው ምድብ ወይም የሲቪል ሰርቪሱ ሠራተኛ ምድብ (civil service employee category) ነው፡፡ ይህ የሰው ኃይል ክፍል ከተሰጠው ስያሜ በቀላሉ መረዳት እንደሚቻለው ለዋናው የዳኝነት ሥራ ድጋፍ የሚያደርጉ ሠራተኞችን የያዘ ምድብ ነው፡፡ ይህ ምድብ የሚተዳደረው ከላይ ከጠቀስነውና ዳኞች ከሚተዳደሩበት ሕግ በይዘቱም ሆነ በዓላማው ፈጽሞ በተለየና በራሱ በፍርድ ቤቱ በወጣ ሕግ ወይም ደንብ ሳይሆን በሌሎች የአስፈጻሚ አካላት በወጣ መመሪያ ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የፌደራል ፍ/ቤቶች የሲቪል ሰርቪሱ ክንፍ የሚተዳደርበት ዋናው የሕግ ማዕቀፍ የፌደራል የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 ነው፡፡[47] በዚህ አዋጅ መግቢያ ላይ በግልጽ እንደምንመለከተው የአዋጁ ዓላማ በሜሪት ላይ የተመሠረተና ብዝሃነትን ያረጋገጠ ጠንካራ የሲቪል ሰርቪስ ሥርዓት መገንባት እንደመሆኑ፣ የመንግሥት ሠራተኞች ቅጥር፣ ደረጃ ዕድገት፣ ዝውውር፣ ስንብት፣ የዲሲፕሊንና ሥነ-ምግባር፣ ደመወዝና ጥቅማጥቅም ዝርዝር ድንጋጌዎች በዚህ መርህ መሠረት የሚተረጎሙና የሚፈጸሙ መሆን አለባቸው፡፡ ይህ ሕግ ተፈጻሚ የሚሆንባቸው እነዚሁ የመንግሥት ሠራተኞች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚወጣ/በወጣ አዋጅ ወይም አስፈጻሚ አካል በሆነው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሠረት በተቋቋመ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በቋሚነት ተቀጥረው የሚሠሩ ሠራተኞች መሆኑን አዋጁ በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ይህም ማለት አዋጁን ተፈጻሚ ለማድረግ በመጀመሪያ ደረጃ መረጋገጥ ያለበት ጉዳይ ተቋሙ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚለውን ትርጉም ማሟላት ይጠበቅበታል ማለት ነው፡፡

አንድ ተቋም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሊባል የሚችለው ከላይ እንደተጠቀሰው በአዋጁ አንቀጽ 2(3) መሠረት *ራሱን ችሎ በአዋጅ ወይም በደንብ የተቋቋመና ከመንግሥት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደር የፌደራል ተቋም* (አጽንኦት የጸሐፊው) ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ተቋሙ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለመባል ሁለት መሠረታዊና ጣምራ መስፈርቶችን ማሟላት ይጠበቅበታል ማለት ነው፡፡ የመጀመሪያው "… *በአዋጅ ወይም በደንብ የተቋቋመ…*" የሚለው ሲሆን ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚወጣ አዋጅ ወይም በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሠረት መቋቋም አለበት፡፡[48]

---

[47] የኢትዮጵያ የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ሕግ እና የሲቪል ሰርቪስ ሥርዓት ረጅም ታሪክ ያስቆጠረ ሲሆን በየዘመኑ በነበሩት የመንግሥት ሥርዓቶችና ርዕዮተ ዓለማዊ ፍልስፍናቸው መለዋወጥን ተከትሎ ሕጎቹም እየተቀያየሩ መጥተዋል፡፡ አሁን ባለንበት ዘመን እንኳ በተለይም ከኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት መውጣትና ከፌደራል ሥርዓቱ መመሥረት በኋላ እንኳ ያለውን ብንቆጥር አሁን ያለው አዋጅ ሦስተኛው ሲሆን ተቋማዊ ማዕቀፉ ደግሞ ለአራተኛ ጊዜ ተቀያይሯል፡፡

[48] በእርግጥ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 34 መሠረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌደራሉን መንግሥት አስፈጻሚ አካላት እንዲያደራጅ (አዲስ ማቋቋም፣ ማጠፍ፣ ማዋሃድ ወይም መክፈል) በግልጽ ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በቀጥታ የአስፈጻሚ አካላትን ማቋቋም አቁሟል፡፡ ይህ አካሄድ በአሁኑ ወቅት ሥራ ላይ ባለው የኢፌዴሪ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2010 አንቀጽ 34 መሠረትም የቀጠለ ነው፡፡

በአንፃሩ ግን፣ ፍርድ ቤቶች በተወካዮች ምክር ቤት በሚወጣ/በወጣ አዋጅ የተቋቋሙ ወይም በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣ ደንብ የተቋቋሙ ሳይሆኑ በቀጥታ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 78(1) መሠረት የተቋቋሙ ናቸው፡፡[49] ሁለተኛው መሥፈርት የበጀት ምደባ ሲሆን ይህ ብዙም የሚያከራክር አይደለም፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ተቋማት በመንግሥት በሚመደብላቸው በጀት የሚተዳደሩ እንደመሆናቸው ፍርድ ቤቶችም በዚሁ ማዕቀፍ ውስጥ የሚካተቱ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም፡፡[50] ስለዚህ ቢያንስ በመጀመሪያው መሥፈርት መሠረት ፍርድ ቤቶች የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚለው ስያሜ ሊሰጣቸው አይገባም በማለት መከራከር ይቻል ይሆናል፡፡

ይህንን አዋጅ እንዲያስፈጽም ሥልጣን የተሰጠው የአስፈጻሚው ኣካል ተቋም (ቀድሞ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር፣ በመቀጠልም የፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር በአሁኑ ሰዓት ደግሞ) የኢፌዴሪ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ነው፡፡ ኮሚሽኑ ከተጣሉበት ተግባርና ኃላፊነቶች አንዱ የሆነውና በአዋጁ ክፍል ሁለት ሥር በአንቀጽ 5(1) የተደነገገው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን አደረጃጀትና መዋቅር የመወሰንና የማጽደቅ ሥልጣን ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች (በተግባር እንደሚታየው የፌደራል ፍርድ ቤቶችንም ጨምሮ) አደረጃጀታቸውን አጥንተውና መዋቅር ሠርተው እንዲሁም በዚሁ ባጠኑት አደረጃጀትና በሠሩት መዋቅር መሠረት የሚያስፈልጋቸውን የሰው ኃይል ብዛት ደልድለው እንዲጸድቅላቸው ለኮሚሽኑ ይልካሉ፡፡

ኮሚሽኑም የቀረበለትን የአደረጃጀት ጥናትና የመዋቅር ጥያቄ የማጽደቅ፣ የማሻሻል ወይም ሙሉ በሙሉ ውድቅ የማድረግ ሥልጣን እንዳለው በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተስማሚ የሆነ የሥራ ምዘና ዘዴ በመምረጥ በማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት (ፌደራል ፍርድ ቤቶችንም ጨምሮ) ተግባራዊ የማድረግ፣ የመንግሥት ሠራተኞችን ደመወዝ ስኬል እና አበል እያጠና በሚኒስትሮች ምክር ቤት የማስወሰን/የማስጸደቅ፣ የመግቢያና የብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት የመዘርጋትና በሚኒስትሮች ም/ቤት የማስወሰን፣ የማስጸደቅና በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ላይ ተግባራዊ የማድረግ፣ የመንግሥት ሠራተኞች ምልመላና መረጣ (ቅጥር፣ ደረጃ እድገትና ዝውውር እንዲሁም ድልድል) መመሪያ ማውጣትና የመንግሥት ሠራተኞችን የዲሲፕሊን ጉዳይ በዳኝነት የማየት ሥልጣንና ኃላፊነቶች ተሰጥተውታል፡፡

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የፌደራል ፍ/ቤቶች የድጋፍ ሰጪው ዘርፍ በዚህ በሲቪል ሰርቪስ ሥርዓት መሠረት በወጡ ሕጎችና ደንቦች እንዲሁም መመሪያዎች የሚተዳደር ነው፡፡[51] ነገር ግን የሲቪል ሰርቪሱ ሠራተኛውን በማስተዳደር ብቻ

---

[49] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 40 የተጠቀሰውን ይመልከቱ፡፡ ከፍርድ ቤቶች በተጨማሪ ሦስቱ ም/ቤቶች (የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት፣ የፌዴሬሽን ም/ቤትና የሚኒስትሮች ም/ቤት) እንዲሁም የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤም በቀጥታ በሕገ መንግሥቱ የተቋቋሙ አካላት ናቸው፡፡

[50] በመሠረቱ ፍ/ቤቶች የመንግሥትን በጀት የሚጠቀሙ ብቻ ሳይሆኑ ለመንግሥትም መጠኑ የማይናቅ ገቢ ከሚያስገቡ ጥቂት ተቋማት ውስጥ የሚመደቡ መሆናቸው ከግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡

[51] ከአዋጅ ቁጥር 1064/2010 በተጨማሪ የመንግሥት ሠራተኞች የቅሬታና የዲሲፕሊን አቀራረብ ሥርዓት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ. 77/1994ን ጨምሮ ኮሚሽኑ ያወጣው

ሳይወሰን የፌደራል ፍርድ ቤቶችን አስተዳደራዊ አደረጃጀትና መዋቅር የመወሰንና የማጽደቅ ሥልጣን ያለው እንደመሆኑ፣[52] ሁለት ጊዜ የፌደራል ፍ/ቤቶች አደረጃጀትና መዋቅር ጥናት ቀርቦለት አጽድቋል፡፡[53] አደረጃጀቱን ማጽደቅ ብቻ ሳይሆን የሥራ መደቦቹ ዓይነትና ደረጃም የሚመዘነውና የሚወጣው በዚሁ ኮሚሽን ስለሆነ አንዳንድ መደቦች በተለይም እንደ ችሎት ጸሐፊ፣ ፋይል ከፋች፣ ትራንስክራይበርና ሌሎች በፍርድ ቤት ብቻ የሚገኙና ከፍርድ ቤት ሥራ ጋር ብቻ የሚገኛኙ መደቦችን ለማስመዘንና የሚገባቸውን ደረጃ ለማሰጠት እጅግ አስቸጋሪ ነበር፡፡ ምክንያቱም የኮሚሽኑ የአሠራር ሂደትና የግንዛቤ ጉዳይ እነዚህን የሥራ ዘርፎች በአግባቡ ተረድቶ ፍ/ቤቱ በሚፈልገውና ብቃት ያለው የሰው ኃይል ሊስብ በሚችል መልኩ ደረጃ እንዲሰጣቸው ማድረጉ ላይ ችግር ስለነበር ነው፡፡[54]

ከዚህ በተጨማሪ በተለያየ ምክንያት በተለይም በአስፈጻሚው አካል ውስጥ የአደረጃጀት ለውጥ ሲኖርና የአስፈጻሚ አካላት መዋሃድ ወይም መክሰምን ተከትሎ ትርፍ የሰው ኃይል ሲኖር ያንን የሰው ኃይል ቦታ ለማስያዝ፣ ኮሚሽኑ ለሁሉም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች (ፌደራል ፍ/ቤቶችን ጭምሮ) ለጊዜው ቅጥርም ሆነ ከሌላ ተቋም የሚደረግ ዝውውርን የከለከለበትም አጋጣሚ እንደነበር ይታወሳል፡፡[55] ኮሚሽኑ ባወጣው መመሪያ መሠረት የተፈጸሙ ቅጥሮች፣ ዝውውሮችና ዕድገቶችን በተመለከተ በየዓመቱ ከኮሚሽኑ የሚላኩ የሰው ሀብት ኦዲትና ኢንስፔክሽን (human resource audit and inspection) ባለሙያዎች ፍርድ ቤቶችን ኦዲት ያደርጋሉ፤

የተሻሻለው የፌደራል መንግሥት ሠራተኞች የምልመላና መረጣ መመሪያን ጨምሮ በርካታ መመሪያዎች ሥራ ላይ ይገኛሉ፡፡

52 አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 5 (1) ይመለከቷል፡፡

53 የመጀመሪያው በ1994 ዓ.ም ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የፌደራል ፍ/ቤቶች እስከአሁን እየተጠቀሙበት የሚገኘውና በ2005 ዓ.ም ጥር ወር ላይ የጸደቀው መዋቅር ነው፡፡ (ከፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ማህደር የተገኘ መረጃ)

54 ከፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኛና ከፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የአስተዳደር ዘርፍ ዋና ዳይሬክተር (ኮርት ማናጀር) ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ (ግንቦት 15 ቀን 2012 ዓ.ም ከረፋዱ 4 ሰዓት ከሩብ በጽ/ቤታቸው)

55 ለምሳሌ የኢፌዴሪ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በመጀመሪያ የኢፌዴሪ መንግሥት በ2011 ዓ.ም ባደረገው የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ማሻሻያ መሠረት በአዋጅ የፈረሱና የተቀላቀሉ የፌደራል ተቋማት በሥራቸው የያዟቸው ሠራተኞችን በተመለከተ በመንግሥት ተቋማት እንዲመደቡ ለማስቻል ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ኅዳር 14 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ፐ/ሰ/ሚ30/ጠ5/14/230 በጻፈው ደብዳቤ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች (ፌደራል ፍ/ቤቶችን ጨምሮ) ቅጥርና ዝውውር የከለከለበትን ሁኔታ ይመለከቷል፡፡ ይህ ክልከላ ለዘጠኝ ወራት ቆይቶ በመስከረም 2012 ዓ.ም ነው የተነሳው፡፡ እስከዛን ጊዜ ድረስ ከኮሚሽኑ በምደባ የተላኩ 2 ሠራተኞች ብቻ ሲሆኑ ፌደራል ፍ/ቤቶች በጣም አስቸኳይ እና አጣዳፊ የሚሏቸውን ቅጥሮች በልዩ ሁኔታ ኮሚሽኑን በደብዳቤ እያስፈቀዱ ከቀጠሯቸው ሠራተኞች ውጪ ቅጥርም ሆነ ዝውውር ሙሉ በሙሉ አቁመው እንደነበር ይታወሳል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም ሚያዚያ 14 ቀን 2012 ዓ.ም ከኮሚሽኑ በተጻፈ ደብዳቤ አሁንም የሰው ኃይል ሽግሽግ ለማድረግ በሚል ምክኒያት ፌደራል ፍ/ቤቶች አዲስ ቅጥርም ሆነ የደረጃ ዕድገት እንዲያቆሙ ኮሚሽኑ ትዕዛዝ ማስተላለፉን ይመለከቷል፡፡ (ከፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ማህደር የተገኘ መረጃ) በተጨማሪም ከፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የሰው ሀብት ሥራ አመራር ቡድን መሪ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ (ሰኔ 3 ቀን 2012 ዓ.ም)

የመመሪያ ጥሰት ተፈጽሟል ብለው ባመኑባቸው ክንዋኔዎች ላይ ግኝት በመመዝገብ ፍርድ ቤቱ እነሱ በሰጡት የማስተካከያና የእርምት አቅጣጫ መሠረት እንዲያስተካክል ትዕዛዝ ይሰጣሉ። በዚህም በሰጡት ትዕዛዝ መሠረት ማስተካከያ ተሠርቶ ሪፖርት ካልተደረገ እርምጃ እስከመውሰድ ድረስ ሥልጣን እንዳላቸው ከተቋሙ አስተዳደር ጋር ከተደረገው ቃለ መጠይቅ በተጨማሪ ከአዋጅ ቁ. 1064/2010 አንቀጽ 94(4)ና አንቀጽ 96(3) መገንዘብና ማረጋገጥ ይቻላል።

ከዚህ በላይ በዝርዝር ለማብራራት እንደተሞከረው ፍርድ ቤቶች የድጋፍ ሰጪ የሰው ኃይላቸውን ያስተዳድራሉ የሚለው ቢኖርም፣ ይህ የማስተዳደር ሥልጣን በሌሎች ሕጎችና ተቋማት በእጅጉ ተሸራርፎ ያለና በሕገ መንግሥቱ የተቀመጠውንና ምሉዕ ሆኖ እንዲተገበር የሚፈለገውን የዳኝነት አካል ተቋማዊና አስተዳደራዊ ነፃነት መርህ በእጅጉ የሚቃረን ነው። አንድን ተቋም እንደ ተቋም መውሰድና ዕውቅና ሰጥቶ ነፃነቱን ማክበር ሲገባ፣ ለውስጥ አሠራር እንዲያመች የተፈጠረውን የድጋፍ ሰጪና የዳኝነት ዘርፍ የሥራ ክፍፍል እንደመነሻ መጠቀም፣ የፍ/ቤቶችን ነፃነት መግፈፍ ሕጋዊና ሕገመንግሥታዊ አይደለም፤ ከሥነ አመክንዮ (logic) ጋርም የሚጋጭ አካሄድ ነው።

ለምሳሌ፣ የቀድሞው የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የራሱን የአስተዳደርም ሆነ ዓላማ አስፈጻሚ ሠራተኞች በራሱ ማለትም ያለ ሲቪል ሰርቪሱ ጣልቃ ገብነት ካቢኔ በሚያወጣለት ደንብ ብቻ እንዲያስተዳድር የማቋቋሚያ አዋጁ ማለትም አዋጅ ቁጥር 587/2000 አንቀጽ 19(1)(ለ) ይፈቅድለታል። በዚህም መሠረት የሚኒስትሮች ም/ቤት በዚሁ ድንጋጌ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ደንብ ቁጥር 155/2000 በማውጣት የሠራተኞቹን አስተዳደር ከመደበኛው የሲቪል ሰርቪስ ሥርዓት ማውጣቱ ይታወሳል።[56] በተመሳሳይ ሁኔታም የፌደራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ከሲቪል ሰርቪስ ሥርዓት ወጥተው በራሳቸው የሚተዳደሩበት ደንብ ቁጥር 8/2010 በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ወጥቶላቸው በዚያ በመተዳደር ላይ ይገኛሉ።

በፍ/ቤቶችም በተመሳሳይ መልኩ ይህንን ችግር ለመፍታት በቅርቡ ሁለት ረቂቅ ሕጎች ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርበዋል። አጠቃላይ የዳኝነት ተቋሙን ለማሻሻል ሁለቱ መሠረታዊ ሕግጋት ማለትም ላለፉት አሥር ዓመታት ሲሠራበት የቆየው የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 684/2002 እና ላለፉት ሃያ አራት ዓመታት ከጥቃቅን ማሻሻያዎች በስተቀር ሥር ነቀል ለውጥ ሳይደረግበት የቆየው የፌደራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 የማሻሻያ ረቂቅ ለፌደራሉ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ተልከዋል። እነዚህ ሁለት ረቂቅ ሕግጋት ካካተቷቸው ለውጦችና አዳዲስ ድንጋጌዎች ውስጥ፣ የፌዴራሉ የዳኝነት አካል ዳኞችን ብቻ ሳይሆን ሌሎች

56 በእርግጥ ለበርካታ ጊዜያት አወዛጋቢ የነበረውና በአንድ ወቅትም ለፌዴሬሽን ም/ቤት ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ቀርቦ ሕገ መንግሥታዊ ነው ተብሎ ጸንቶ የነበረው የደንቡ አንቀጽ 37 በቅርቡ ማለትም የካቲት ወር 2011 ዓ. ም. በድጋሚ ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ቀርቦ ከሕገ መንግሥቱ ጋር የሚጣረስ ድንጋጌ እንደሆነ በመስማማት የውሳኔ ሓሳቡን ለፌዴሬሽን ም/ቤት አቅርቦ ም/ቤቱም በሙሉ ድምጽ ድንጋጌውን ብቻ በመለየት እንዲሻር ወስኗል።

የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞቹንም አስተዳደር በሚመለከት ደንብ የማውጣት ሥልጣን የሚሰጡት ድንጋጌዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡[57]

### 4.2 የፌደራል ፍ/ቤቶች የበጀትና የንብረት አስተዳደር

ሌላው ሕገ መንግሥቱና አዋጁ ካስቀመጡት መርህ ጋር የሚጣረሰው የፌደራል ፍርድ ቤቶች የበጀት ነፃነትና አስተዳደር ጉዳይ ነው፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ለሥራ ማስኬጃና የፌደራል ፍርድ ቤቶችን ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን በጀት በማዘጋጀት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በቀጥታ በማቅረብ እንደሚያስወስንና ሲፈቀድም በሥራ ላይ እንደሚያውል በሕገ መንግሥቱም ሆነ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ላይ በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡[58] ይህ ድንጋጌ በሕገ መንግሥቱ በዚህ መልኩ እንዲደነገግ የተደረገው ፍርድ ቤቶች በጀታቸውን በቀጥታ ለምክር ቤት አቅርበው ያለምንም ውጣ ውረድ እንዲፈቀድላቸውና በዚህም የዳኝነትን ነፃነት ለማረጋገጥና የዳኝነት ሥራ በተቀላጠፈ መንገድ እንዲከናወን ይረዳ ዘንድ ታስቦ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡[59] ከላይ እንደተገለፀው በዚህ ረገድ ሀገራት የተለያየ ልምድ ያላቸው ሲሆን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 79(6) ጋር ሊጣጣም የሚችለው የጥቅል በጀት አፈቃቀድ (consolidated fund/budget) ስልት ነው፡፡ ይህም ማለት ለምሳሌ ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ ዘርፍ ከሀገሪቱ ጥቅል በጀት እንደየሁኔታውና እንደየጊዜው የሚሻሻል በመቶኛ ይህን ያህል በጀት ተይዟል እንደሚባለው በተመሳሳይ ከሀገሪቱ አጠቃላይ በጀት በጥቅሉ (በአስፈላጊነት ጥናት የተደገፈ) ለዳኝነት ዘርፉም ሊያዝ የሚገባው መሆኑን ነው፡፡

በሥራ ላይ ያለው አተገባበር ግን ከዚህ የተለየና ከሕገ መንግሥቱም ሆነ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 ጋር የተጣረሰ ነው፡፡ የፌደራል ፍርድ ቤቶች የበጀት ጥያቄያቸውን ከማቅረባቸው በፊት በመጀመሪያ የበጀት ጣሪያቸው ምን ያህል እንደሆነ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ገንዘብ ሚኒስቴር ትሬዠሪ ዘርፍ ይገለጽላቸዋል፡፡[60] ከዚያም በዚሁ በተሰጣቸው ጣሪያ መሠረት የፍርድ ቤቶች የበጀት ጥያቄ በሕገ መንግሥቱና በአዋጁ መሠረት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሳይሆን ለገንዘብ ሚኒስቴር ይቀርባል፡፡ ሚኒስቴሩም በሚወስነው ቀንና ቦታ የበጀት ማስረዳት (budget defense session) መድረክ ተዘጋጅቶ የፌደራል

---

57 የፌደራል ዳኝነት አስተዳደር ረቂቅ አዋጅ አንቀጽ 8(14) እና የፌደራል ፍርድ ቤቶች ረቂቅ አዋጅ አንቀጽ 23(2) እና አንቀጽ 38ን ይመለከቷል፡፡ ነገር ግን እንደ ጸሐፊው እምነት እነዚህ ረቂቅ ሕግጋትም ቢሆኑ በመካከላቸው የሥልጣን መደራረብና መጣረስ ስለሚስተዋል ሊስተካከሉ ይገባል፡፡

58 የኢ.ፌ.ዲ. ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 79 (6) እና የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁ. 25/1988 አንቀጽ 16 (2) /ሐ/ ይመለከቷል፡፡

59 የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ጉባኤ ቃለ ጉባኤ ቁጥር 27 እና 28 / ኅዳር 21-24 1987 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ/ ገጽ 19 እና 21 ይመለከቷል፡፡

60 የኢፌዲሪ ገንዘብ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1097/2010 አንቀጽ 16(1)/ሠ/ እና /ሰ/ አማካኝነት በተሰጠው *ሥልጣን መሠረት የፌደራል መንግሥትን የበጀት፣ የሒሳብ አያያዝ፣ የክፍያና የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፡፡ የፌደራል መንግሥቱን በጀት ያዘጋጃል፡፡ በተፈቀደው በጀት መሠረት ክፍያ ይፈጽማል፡፡ የበጀቱን አፈጻጸም ይገመግማል፡፡ ይህንንም ተከትሎ ሚኒስቴሩ ለሁሉም የመንግሥት ተቋማት* (ፍርድ ቤቶችንም ጨምሮ) በተሰጠው የበጀት ሥርዓት መዘርጋት ሥልጣን መሠረት የተመደበላቸውን የበጀት ጣሪያ ይልካል፡፡ ማንኛውም ተቋም ከዚሁ ከተቀመጠለት የበጀት ጣሪያ በማለፍ የበጀት ጥያቄ ማቅረብ አይችልም፡፡

ፍርድ ቤቶች አመራሮች ከሌሎች የፌደራል አስፈጻሚ ተቋማት ጋር በመሆን ያቀረቡትን የበጀት ጥያቄ ምክንያታዊነት ለሚኒስቴሩ ወይም እርሱ ለሚሰይመው አካል ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡ ለሚቀርብላቸውም ጥያቄ በቂና አሳማኝ መልስ እንዲሰጡ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ይህ ሂደት ካበቃ በኋላ ሚኒስቴሩ የቀረበውን ማብራሪያና የተሰጡትን ምላሾች ተቀብሎ ካመነባቸው የቀረበውን የበጀት ጥያቄ በማሻሻል ወይም እንዳለ በመቀበል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከሚቀርበው አጠቃላይ በጀት ውስጥ እንዲካተት ያደርጋል፡፡ በተቃራኒው የተሰጠውን ማብራሪያና ምላሽ ሚኒስቴሩ ካልተቀበለ የቀረበውን የበጀት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ፣ በራሱ አስተያየትና የፌደራል ፍርድ ቤቶችን ያለፈ የበጀት አፈጻጸም መሠረት በማድረግ በቂ ነው ብሎ ያሰበውን በጀት እንዲመደብ ያደርጋል፡፡[61] ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ሁኔታ ሕገ መንግሥቱም ሆነ አዋጁ ካስቀመጠው ውጪ በአስፈጻሚው አካል ተወስኖና ተፈቅዶ የተመደበው በጀትም ሙሉ በሙሉ በቀጥታ ወደ ፌደራል ፍርድ ቤቶች የባንክ ሒሳብ መግባት ሲገባው በሦስቱም ፍርድ ቤቶች የበጀትና ፋይናንስ ዳይሬክተሮች በየወሩ ስላለፈው ወር አፈጻጸም ሪፖርት ካቀረቡ በኋላ ብቻ ለቀጣይ ወር የሥራ ማስኬጃ በጀት ይለቀቅላቸዋል ወይም ወደ ባንክ ሒሳባቸው እንዲገባ ይደረጋል፡፡[62]

በዚህ ጉዳይ ሚኒስቴሩ ብዙ ጊዜ የሚሰጠው ምክንያት የሀገሪቱ የበጀት ቋት አንድ መሆኑንና ይህንንም ቋት ለማስተዳደር በአዋጅ ሥልጣን የተሰጠው መሆኑን ነው፡፡[63] ነገር ግን፣ አንደኛ፣ በሕገ መንግሥቱና በአዋጁ በተገለፀው መርህ መሠረት ሚኒስቴሩ ጣልቃ የመግባትም ሆነ የማዘዝ ሥልጣን የሌለው በመሆኑ፣ ሁለተኛ፣ በምክር ቤቱ እንዲፈቀድ የተባለው በጀት የግድ የተለየ ቋት የሚያስፈልገው ሳይሆን በጥቅል በጀት መልክ ከጠቅላላው የሀገሪቱ በጀት ላይ ተቆርሶ እንዲመደብ ማድረግ የሚቻል በመሆኑ በሚኒስቴሩ በኩል የሚቀርበው ምክንያት ብዙም የሚያሳምን አይደለም፡፡

ከሌሎች ሀገራት ልምድ በተጨማሪ በዚሁ በሀገራችን የክልሎችን ልምድ እንኳ ብንመለከት ለምሳሌ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በሥሩ የሚገኙትን የ22 የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤቶችና የ304 የወረዳ ፍ/ቤቶች የሚያስተዳድርበት በጀት በጥቅሉ ለክልሉ መንግሥት ከሚመደበው በጀት 2.1 በመቶ ሲሆን ይህም በጥቅል በጀትነት ከክልሉ መንግሥት ያለ ፋይናንስ ቢሮ ጣልቃ ገብነት ተመድቦለት

---

61 በዚህ መልኩ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትን ብቻ እንደ ምሳሌ ብናነሳ ለ2010 ዓ. ም 264,327,320 ብር ተጠይቆ በሚኒስቴሩ የተፈቀደው ግን 87,730,000 ብር ነው፡፡ ለ2011 በጀት ዓመት የተጠየቀው ደግሞ ብር 171,062,104 ሲሆን በሚኒስቴሩ የተፈቀደው ግን ብር 94,034,000 ብቻ ነው፡፡ ለ2012 በጀት ዓመትም ተጠይቆ የነበረው የበጀት ብር መጠን 126,425,907 ሲሆን በሚኒስቴሩ የተፈቀደው ግን ብር 125,000,000 ነው፡፡ ለ2013 ዓ. ምም የተጠየቀው የበጀት መጠን ብር 211,425,800 ሲሆን የተፈቀደው ግን ብር 165,195,028 ብቻ ነው፡፡ (ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፋይናንስና በጀት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 9 ቀን 2012 ዓ.ም)

62 ዝኒ ከማሁ

63 ዝኒ ከማሁ

ይሠራል፡፡[64] በሌሎች ክልሎችም ቢሆን የመቶኛው መጠን ይለያይ እንጂ የበጀት አመዳደብ ሥርዓት ከኦሮሚያ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡[65]

ሌላው ከበጀትና ከፋይናንስ አስተዳደር ነፃነት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ፍርድ ቤቶች የውስጥ ገቢያቸውን በመጠቀም ይህን ገቢ ለውስጥ አቅም ማጠናከሪያ እንዲያውሉ የማስቻል አስፈላጊነት ነው፡፡ ሌሎች ተቋማት መንግሥት ከሚመድብላቸው መደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት በተጨማሪ ከተለያዩ ምንጮች የሚያገኟቸውን ገቢዎች ያለውን መዋቅርና የሥልጣንና የአሠራር ተዋረድ በመከተል እያስፈቀዱ መጠቀም የሚችሉበት የሕግ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡[66] በዚህ ረገድ፣ ከፍተኛ የመንግሥት የትምህርት ተቋማትን (ዩኒቨርሲቲዎችን) ለአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ፍርድ ቤቶችም በርካታ የውስጥ ገቢዎች ያሏቸው ሲሆን በተለይም በፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ወይም ክርክሮች ላይ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 215 (1) መሠረት የሚከፈለው የዳኝነት ክፍያ (court fee) ትልቁን ድርሻ ይወስዳል፡፡[67] የዳኝነት ክፍያ ፍርድ ቤቶች ለሚሰጡት የዳኝነት አገልግሎት የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ ሲሆን በፍትሐ ብሔር ክሱ ውስጥ የተመለከተው የገንዘብ መብት ጥያቄን መሠረት አድርጎ የሚወሰን ነው፡፡ በዚህም የፌደራል ፍ/ቤቶች በየዓመቱ ከዳኝነት ክፍያ ከፍተኛ ገቢ ለመንግሥት ፈሰስ ያደርጋሉ፡፡[68] ሆኖም ግን ይህ የውስጥ ገቢ ለሌሎች ተቋማት በተፈቀደውና በተዘረጋው የሕግ ሥርዓት ልክ ለፌደራል ፍርድ ቤቶች ተግባራዊ አልተደረገም፡፡

---

64 ከቀድሞ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የዕቅድና በጀት መምሪያ ኃላፊ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፣ ዓርብ ታህሳስ 23 ቀን 2013 ዓ.ም.

65 ዝኒ ከማሁ

66 በዚህ ረገድ የኢፌዴሪ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2010 አንቀጽ 14(15) እና በኢፌዲሪ መከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁ. 1100/2011 አንቀጽ 69(2) መሠረት የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴር ከተለያዩ የውስጥ ምንጮች የሚያገኘውን ገቢ በሕግ መሠረት እያስፈቀደ ሊጠቀም እንደሚችል በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከፍተኛ የመንግሥት ትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲዎች) መንግሥት ከሚመድብላቸው ጥቅል በጀት በተጨማሪ ሕጋዊ ሥርዓቱን ተከትለው የውስጥ ገቢ ፈንድ በማቋቋም ራሳቸው ያመነጩትን ገቢ መጠቀም እንደሚችሉ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 67 የተደነገገ ሲሆን ይህ አዋጅ ከመጽናቱም በፊት የተለያዩ የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢያቸውን የመጠቀም ሥልጣን የተሰጣቸው መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ለምሳሌ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁ. 60/1992 አንቀጽ 14፣ የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁ. 61/1992 አንቀጽ 14፣ የደቡብ (የዛሬው ሃዋሳ) ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁ. 62/1992 አንቀጽ 14 እና የጅማ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁ. 63/1992 አንቀጽ 14ን መመልከት ይቻላል፡፡

67 ከዚህ በተጨማሪ ከተለያዩ ቅጣቶች፣ ከዋስትና ገቢዎች፣ ከፍርድ አፈጻጸም ሂደቶች እንዲሁም ሌሎች ምንጮች ፌደራል ፍርድ ቤቶች ከፍተኛ ገቢ ለመንግሥት ያስገባሉ፡፡

68 ለምሳሌ በ2012 ዓ.ም ከፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ብቻ ከዳኝነትና ከሌሎች አገልግሎቶች የተሰበሰበና ለመንግሥት ገቢ የተደረገ የብር መጠን 16,147,003.02 (አሥራ ስድስት ሚሊዮን አንድ መቶ አርባ ሰባት ሺ ሶስት ብር ከሁለት ሳንቲም) ነው፡፡ (ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፋይናንስና በጀት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 9 ቀን 2012 ዓ.ም.)

ፌደራል ፍርድ ቤቶች በበጀትና ፋይናንስ አስተዳደራዊ ነፃነት ብቻ ሳይሆን በንብረት አቅርቦት ግዢም ሆነ በንብረት ማስወገድ ጉዳይ ከአስፈጻሚው ጥገኝነት የተላቀቁ አይደሉም፡፡ በዚህም ረገድ በማዕከላዊነት የንብረትም ሆነ የተለያዩ አገልግሎቶችንና ግንባታዎችን ግዢና የንብረት ማስወገድ ሥራ እንዲያከናውኑ የተቋቋሙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ያሉ ሲሆኑ እነዚህም የመንግሥት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲና የመንግሥት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ተቋም ናቸው፡፡[69] ለፌደራል ፍርድ ቤቶች ከሚመደበው ዓመታዊ በጀት ውስጥ ከ60 በመቶ በላይ የሚውለው ለተለያዩ ዓይነት ግዢዎች ሲሆን፣ ይህም ዓመቱን ሙሉ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡[70] ሆኖም ግን ማንኛውም የግዢ ሥራዎች የሚካሄዱት (አዋጁ በሚያስቀምጠውና በአዋጁ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት) የገንዘብ ሚኒስቴርና የግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በሚያወጧቸው መመሪያዎች መሠረት በመሆኑ፣ ፌደራል ፍርድ ቤቶች ለዳኝነት አገልግሎት የሚውሉ የሎጅስቲክስ እና ሌሎች ቁሳቁሶች ወይም የምክር አገልግሎቶች ወይንም ግንባታዎች ለመግዛት ረጅምና ውጣ ውረድ የበዛበት አካሄድ ለመሄድ ይገደዳሉ፡፡

ለምሳሌ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች እንደ ድምጽ መቅረጫ ማሽን፣ ካሜራ፣ ሲሲቲቪ፣ ኮምፒዩተር ዴስክ ቶፕ፣ ላፕቶፕና ሌሎች ቁሳቁሶች አጀንሲው በራሱ ጨረታ አውጥቶ ተዋውሎና ዋጋ ተምኖ ለሦስት ዓመት ውል በመፈጸም ጨረታውን ካሸነፈው ድርጅት ግዢ እንዲፈጽሙ ለሁሉም የመንግሥት ተቋማት (ፍርድ ቤቶችን ጨምሮ) መረጃውን ይልካል፡፡ ነገር ግን የተባለው ድርጅት ምንም እንኳን ጨረታውን ያሸነፈ ቢሆንም የተለያዩ ምክንያቶችን በመፍጠር ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን ለማቅረብ ፈቃደኛ ሳይሆን ወይም ሳይችል የሚቀርባቸው ጊዜያት በርካታ ናቸው፡፡ ይህንንም ለኤጀንሲው በማሳወቅ መፍትሔ እንዲያቀርብ ሲጠየቅ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ ከወጡት ድርጅቶች ግዢው እንዲፈጸም ትዕዛዝ ያስተላልፋል ወይም በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ የባከነው ጊዜ ከግምት ውስጥ ሳይገባ ኤጀንሲው ተቋማት በራሳቸው ጨረታ አውጥተው እንዲገዙ የመጨረሻ ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡[71]

በጊዜውና በታቀደው መሠረት በተለይም ለዳኝነት አገልግሎት የሚውሉ ቁሳቁሶችን በወቅቱ በማቅረብ ሂደት ላይ የሚፈጠረው ችግርና የዕቅድ መዛባት ፍትህ በመስጠት አገልግሎት ላይ የሚያስከትሉት መጓተትና ቅሬታ ግልጽ ነው፡፡ ምክንያቱም ፍ/ቤቶች የሚሰጡት የዳኝነት አገልግሎት ለጥቂት ሰዓታትም እንኳ ሊቋረጥ የማይገባው እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህ አገልግሎት ቢቋረጥ በዚሁ ምክንያት ብቻ ቀጠሮዎች ይራዘማሉ፣ ባለጉዳዮች ለተጨማሪ ወጪና ጊዜ እንዲሁም ጉልበት ይዳረጋሉ፤ በማረፊያ ቤት የሚገኙ ተከሳሾች በተራዘመ ቀጠሮ ምክንያት ሊያገኙ የሚገባቸው ፍትሕ ይዘገያል፡፡ ስለዚህ ለፍርድ ቤቶች ሎጅስቲክስ እና ሌሎች አገልግሎቶች መሟላት ከሌሎች ተቋማት በላይ ቅድሚያ ሊሰጥ ወይም በራሳቸው ግዢ የሚያከናውኑበት ሁኔታ ሊፈጠር ሲገባ፣ አሁን ያለው መጓተት ከውስጥ አቅም ውሱንነት ጋር ተደምሮ ለፍርድ ቤቶች አገልግሎት አሉታዊ ነው፡፡

---

69 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግሥት ግዢና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ይመለከቷል፡፡

70 ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግዢና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ (ሰኔ 10 ቀን 2012 ዓ.ም)

71 ዝኒ ከማሁ

በንብረት ማስወገዱም በኩል ያለው ተመሳሳይ ችግር ነው፡፡ ከላይ በተገለፀው አካሄድ እንደ መከላከያ ባሉ ተቋማት ሕጋዊ ሥርዓት ተበጅቶላቸው የራሳቸውን ግዢ ራሳቸው እንዲፈጽሙ እና እንዲያስወግዱ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡[72] ይህ የተደረገው የመከላከያ ጉዳይ የሀገር ደህንነትና ሰላም እንዲሁም የሕዝብን ፀጥታ የማስከበር ጉዳይ በመሆኑ ነው፡፡[73] በመሠረቱ ይህ አሠራርና መነሻ ምክንያቱ አግባብነት አላቸው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም፣ የሀገር ደህንነትና ሰላም እንዲሁም የሕዝብ ፀጥታና መረጋጋት ከውጭ ሊመጣ ከሚችል ወረራ ወይም ጥቃት ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን፣ ከሕግ የበላይነትና የዜጎች መብት መረጋገጥ ጋር ተያያዥነት ያለው በመሆኑ ፍርድ ቤቶችን በሚመለከት የሚነሳው የአቅምና የነፃነት ጥያቄ በቂ ምላሽ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

በመሠረቱ አዲስ በተዘጋጀው የፌደራል ፍርድ ቤቶች ረቂቅ አዋጅ አንቀጽ 35(1) ላይ በግልጽ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ከመንግሥት በጀት ላይ ጥቅል የሆነ የፍርድ ቤት ፈንድ ይመደብላቸዋል የሚል ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ይህም ከላይ በዝርዝር ለማስቀመጥ እንደተሞከረው መሠረታዊ የሆነውን የፍርድ ቤቶችን የበጀት ነፃነት ጥያቄ የሚፈታ መሆኑ ቢታመንበትም የፌደራል ፍርድ ቤቶችን የውስጥ ገቢ አጠቃቀም በተመለከተ ረቂቅ አዋጁ ያለው ነገር የለም፡፡ በተጨማሪም ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የፌደራሉ የዳኝነት አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅም ሆነ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ረቂቅ አዋጅ በረቂቅነት ደረጃ ላይ ያሉ እንደመሆኑ፣ የዳኝነት ተቋሙን አስተዳደራዊና መዋቅራዊ ነፃነት ለማስጠበቅ እና ለማስከበር ገንቢ ሚና ገና መጫወት አልጀመሩም፡፡

### 4.3 ሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮች

የፌደራል ፍርድ ቤቶች ከላይ ባየናቸው ዋና ዋና የሰው ኃይል፣ የበጀት፣ የግዢና ንብረት አስተዳደር ጉዳዮች ብቻ ሳይሆን በሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮችም ሕገ መንግሥታዊ የሆነው ተቋማዊ ነፃነታቸው እንዲጣስ ተደርጓል፡፡ በዚህ ረገድ በዋነኛነት የሚጠቀሱት አንደኛ እንደ ተቋም የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል መመሪያ ለማውጣት ፍርድ ቤቶች ያላቸው ሥልጣንና፣ ሁለተኛ፣ ከአደረጃጀት ጋር ተያይዞ የሚነሳው የውስጥ ኦዲት ሥራን የሚመለከት ነው፡፡

በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 16(1) ላይ በግልጽ እንደተደነገገው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚደንት በሕግ መሠረት የፌደራል ፍርድ ቤቶችን ለማስተዳደር ኃላፊ ይሆናል፡፡ ይህም የሚያሳየው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደ አንድ ማንኛውም ተቋም መሪ የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ በማቀድ፣ በማደራጀት፣ ብቃት ያለው የሰው ኃይል በመመደብ፣ አመራር በመስጠትና ድጋፍና ክትትል በማድረግ የማስተዳደር ሥልጣን እንደተሰጠው ነው፡፡ ማስተዳደርን (administration) ከማቀድ ጀምሮ እስከ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ድረስ ካሉት የሥራ አመራር (management) ሂደቶች ውጪ ማሰብ አይቻልም፡፡ ይህንን ኃላፊነቱን ለመወጣት ደግሞ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚደንት መመሪያ ማውጣት እንደሚያስፈልገው እሙን ነው፡፡

የፌደራል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ ቁ. 25/1988 ባሻሻለው አዋጅ ቁ. 454/1997 አንቀጽ 2(4) መሠረት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሥራ ላይ ያሉ ሕጎችን ሳይቃረን አስፈላጊ የሆኑ የሥነ ሥርዓት መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን እንዳለው

[72] በኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁ. 1100/2011 አንቀጽ 70ን ይመለከቷል፡፡

[73] የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሥት ግዢና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 3(2) እና የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁ. 1100/2011 አንቀጽ 70 እና 71ን ይመለከቷል፡፡

ተደንግጓል፡፡[74] ነገር ግን፣ በተግባር እንደሚታየው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከላይ በተጠቀሱት የሕግ ማዕቀፎች መሠረት አስተዳደራዊ መመሪያዎችን ለማውጣት በሚሞክርበት ወቅት ፍ/ቤቶች መመሪያ ማውጣት ሥልጣን እንደሌላቸው የሚገልጽና፣ በዚህ ረገድ ያላቸው ሥልጣን ለሌሎች የአስፈጻሚ አካላት በመላክ ማስጸደቅ እንጂ በራሳቸው የማስፈጸም ሥልጣን የላቸውም የሚል ከፍተኛ ተቋውሞ ይቀርባል፡፡[75] በመሠረቱ ይህ ሥልጣን በቂ፣ ሁሉ-አቀፍና ግልጽ የሆነ ሕግ ማዕቀፍ የሚያስፈልገው ቢሆንም፣ ከላይ የተጠቀሱት የሕግ ማዕቀፎችን በመጠቀም እንደ አንድ ራሱን የቻለ ተቋም መመሪያ በማውጣት ሥራዎችን ማከናወን መቻልና ተቋሙን ለመምራት መንቀሳቀስ ሊያስመሰግንና እንዲታገዝ ሊያደርግ የሚችል እንጂ ሊያስወቅስ የሚገባው አልነበረም፡፡

ሁለተኛው ጉዳይ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ውስጥ የሚገኘው የውስጥ ቁጥጥር (ኦዲት) ሥርዓትና አደረጃጀት ነው፡፡ በመሠረቱ በፌደራል ፍ/ቤቶች ብቻ ሳይሆን በማናቸውም ዘመናዊ የአስተዳደርና አደረጃጀት ሥርዓት በሚከተሉ የግልም ሆነ መንግሥት ተቋማት ውስጥ በሥራ አመራርና ተቋማዊ አደረጃጀት ሳይንስና መርህ (modern organizational management science and principles) መሠረት ሥራዎችን ለይቶ፣ ዘርዝሮና አደራጅቶ በማከፋፈልና የውስጥ የሥራ ክፍሎችን በማደራጀት መምራት የሚገባ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህንንም በመከተል የፌደራል ፍ/ቤቶች በ1994 ዓ.ም. ከዚያም በ2005 ዓ.ም. ተቋማዊ አደረጃጀታቸውን አጥንተውና አዘጋጅተው ለሚመለከተው አካል በመላክ አስጸድቀው ሥራ ላይ አውለዋል፡፡ ሆኖም ግን በ2008/2009 ዓ.ም ከገንዘብ ሚኒስቴር በተላለፈ ሰርኩላር፣ ከዚያም ይኸው ሰርኩላር የኢፌዲሪ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2010 አንቀጽ 16(1)(ሰ) ተጠናክሮ የገንዘብ ሚኒስቴር "የፌደራል መንግሥትን የበጀት፣ የሒሳብ አያያዝ፣ የክፍያና የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ይዘረጋል፣ የአፈጻጸሙን ውጤታማነት ይከታተላል፤" በሚል ተደንግጓል፡፡

ይህን መነሻ በማድረግ፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተርም ሆነ ሌሎች የሥራ ክፍሉ ሠራተኞች ቅጥር፣ ምደባ፣ እድገት፣ ዝውውርና የሥራ አፈጻጸም ሥራ የሚከናወነው የሥራ ክፍሉ በተቋቋመበትና በሚገኝበት በፍርድ ቤቱ መዋቅር ሳይሆን በገንዘብ ሚኒስቴር ነው፡፡ ለዚህም የተሰጠው ምክንያት ከዚህ በፊት የአንዳንድ ተቋማት የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች የተቋማቸውን የሒሳብ አያያዝ ችግርና ጉድለት በማሳየታቸው በተቋማት የበላይ ኃላፊዎች ከሥራ እስከመፈናቀል ድረስ የሚደርስ በደልና ተጽእኖ ስለደረሰባቸው

74 ይህ የአዋጁ ድንጋጌ በግልጽ እንደሚያስቀምጠው ፍ/ቤቱ የሥነ ስርዓት መመሪያዎች እንደሚያወጣ ቢሆንም የሥነ ስርዓት መመሪያ ማለት ምን ማለት ነው? ምን ምን ጉዳዮችንስ ነው የሚሸፍነው? የሚሉት ጥያቄዎች አወዛጋቢነት እስካሁን ድረስ ቀጥሏል፡፡

75 ለምሳሌ በ2011 ዓ.ም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፌደራል ፍ/ቤቶች ተፈጻሚ የሚሆን የፌደራል ፍ/ቤቶች ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች የሥራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ መመሪያ ለማውጣት እና ወጥ ተቋማዊ ሥርዓት ለመዘርጋት ባደረገው ጥረት ከቀረቡት ተቃውሞዎች አንዱ ይኸው መመሪያ ማውጣት ሥልጣን ጉዳይ ነበር፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ፌደራል ፍርድ ቤቶች የተከሳሾችን ሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ ለማስከበር እንዲረዳቸው የችሎት ቋንቋ አስተርጓሚ አበል አከፋፍልን በተመለከተ ወጥነት ያለው መመሪያ በሚዘጋጅበት ጊዜ ዋነኛ የክርክር ምክንያቶች ከነበሩት ውስጥ አንዱ ይኸው የፍርድ ቤቶች በተለይም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መመሪያ የማውጣት ሥልጣን ጉዳይ ነው፡፡

ይህንኑ ለመቅረፍና የኦዲት ሥራ ክፍሎችን ነፃነትና ደህንነት ለማረጋገጥ የሚል ነው፡፡

በመሠረቱ የኦዲት ሥርዓት ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው፣ ተቋማት የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግተው የገንዘብ፣ የአፈጻጸምና የንብረት ሥርዓታቸውን ግልጽ፣ ከብክነት የፀዳ እና ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ ማንኛውም የተቋም አመራር/ባለሥልጣን ወደ ኃላፊነት ሲመጣ ወይም በዚያ ከፍተኛ የአመራር ቦታ ሲመደብ ይህንን ተግባር በኃላፊነት መንፈስ እንደሚወጣ፣ እንዲሁም በተጠያቂነትና በአገልጋይነት መንፈስ እንደሚሠራ ታምኖበት ሊሆን ይገባል፡፡ ስህተትና ጉድለት በማሳየት የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ምክረ ሐሳብ የሚያቀርብን ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ማበረታታትና መደገፍ፣ እንዲሁም በውስጥ ኦዲት መረጃ መሠረት እርምጃ በመውሰድ ስህተትን ማስተካከል የማንኛውም የሥራ ኃላፊ ግዴታ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ሳይሆን ቀርቶ ኃላፊነቱን በአግባቡ በተወጣው የውስጥ ኦዲት ኃላፊ ወይም ባለሙያ ላይ በተቃራኒው ሕገ ወጥ እርምጃ የሚወስድ የተቋም ኃላፊ ወይም አመራር ከኃላፊነት እንዲነሳ በማድረግ የተቋሙን ነፃነትና ተጠያቂነት በተጓዳኝ ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት ይገባል፡፡ ከዚህ ግልጽ መፍትሔ ይልቅ፣ በፌዴራል ፍ/ቤቶች የውስጥ አስተዳደራዊ ሥራ ላይ የአስፈፃሚውን ጣልቃ ገብነት በሚያጎላ መልኩ አንድን የሥራ ክፍል ነጥሎ ለሌላ አካል ተጠሪ ማድረግ ሊስተካከል የሚገባው መሠረታዊ ስህተት ነው፡፡

የፌደራል ፍርድ ቤቶች በተለይም አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ለመስጠት ሥልጣን የተሰጠው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ሚና ሊኖረው ይገባል የሚል እምነት ቢኖርም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች እስከዛሬ በሚሰጧቸው ውሳኔዎች የዳኞችን ግለሰባዊ/ውሳኔያዊ ነፃነት በሚያረጋግጥ መልኩ እንጂ ተቋማዊ ነፃነቱን በተመለከተ አቋም ሲይዙ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ውሳኔያቸው ላይ ሲያንፀባርቁ ብዙም አይስተዋልም፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት የሚነሳው ምንም እንኳ በዳኞችም ሆነ በችሎቶቹ የፌደራል ፍ/ቤቶች ተቋማዊ ነፃነት ሊጎናጸፉ እንደሚገባ ግንዛቤው ቢኖርም፣ ፍ/ቤቶች ተቋማዊ ወይም አስተዳደራዊ ነፃነታቸው ሊረጋገጥ የሚችለው በሕግ እና በአደረጃጀት እንጂ ችሎቱ በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ወይም ችሎቱ በውሳኔው በሚይዛቸው አቋሞች ሊሆን አይችልም የሚል እምነት ስላለ እንደሆነ ይጠቀሳል፡፡[76]

## መደምደሚያ

ከላይ በመግቢያው መጀመሪያ ላይ የተጠቀሰውና ለኢትዮጵያ ዘመናዊ ሕጎች እንደመነሻ የሚወሰደው ፍትሐ ነገሥት ብሔረ ሕግ ወቀኖናት፣ "ዳኛ ነፃነት ያለው ይሁን፤ ራሱን ለማስተዳደር ሥልጣን ያለው ያልሆነ ሰው ሌሎቹን ሊያስተዳድር አይቻለውምና" በማለት ያስቀመጠው ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ የዳኝነት ነፃነት ሲባል የዳኞች ከማንኛውም አካል ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆነው በሕግና በህሊናቸው ብቻ ይመራሉ ማለት ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ በዋነኛነት እነዚሁ ዳኞች የሚሠሩበት ተቋም አስተዳደራዊ ነፃነት ከሌለውና በሌሎች በተለይም በአስፈጻሚው አካል ላይ በእጅጉ ጥገኛ ከሆኑ ሥራቸውን በአግባቡ ሊያከናውኑና ጥራት ያለው ዳኝነት በቀላጠፈ

[76] ከፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኛ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፣ ሐሙስ ታህሳስ 22 ቀን 2013 ዓ.ም.

መንገድ ሊሰጡ እንደማይችሉ እሙን ነው፡፡ በአሁኑ ወቅትም የዳኝነት ሥርዓቱን ሥር ነቀል በሆነ መልኩ ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት ከላይ በችግርነት የተጠቀሱትን የሰው ኃይል አስተዳደር፣ የበጀትና ንብረት አስተዳደር፣ የውስጥ ቁጥጥርና ተቋማዊ አደረጃጀት ጉዳዮች ከአስፈጻሚው አካል ነፃ ሆነው፣ በሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ደረጃ የሕግ ማዕቀፉን በማሻሻል የፍርድ ቤቶችን ነፃነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን የዳኝነት ተቋማዊ ነፃነት መገለጫ ጉዳዮች አዲስ በሚሻሻሉትና የፍ/ቤቶችን ነፃነት በተሻለ መንገድ ያስከብራሉ በተባሉት ሁለት ረቂቅ አዋጆች ውስጥ አንድ በአንድ በመርህ መልክ ማካተት የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም የሕግ አውጭው አካል ወሳኝና የማይተካ ሚና አለው፡፡ የአስፈጻሚው አካልም የዳኝነት ነፃነት ሕገ መንግሥታዊ መርህ መሆኑን በመገንዘብ እና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መዳበር ረገድ ትልቁን ድርሻ እንደሚወስድ በማጤን ትርጉም ያለው ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ሊያሳይ ይገባል፡፡ ያንኑ ያህል ደግሞ፣ ፍ/ቤቶች ነፃነታቸውን በማስከበርና በማስጠበቅ ረገድ ጉልህ ሚና አላቸው፡፡

በአሁኑ ወቅት አዋጅ ቁጥር 25/1988 እና ተከታዮቹን ማሻሻያ አዋጆች በሙሉ የሚተካ አዲስ የፌደራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ረቂቅ ሰፊ ውይይትና ግብዓት ተጨምሮበት ከመጽደቅ ጫፍ ላይ ደርሷል፡፡ ይህ የሕግ ረቂቅ በርካታ አዳዲስ ምናልባትም በፍ/ቤቶች ታሪክ የመጀመሪያ ሊባሉ የሚችሉ የአሠራርና የአደረጃጀት ለውጦችን የያዘ ሲሆን በዚህ ጽሑፍ የተሰነዘሩትን አብዛኛዎቹን አስተያየቶችና የመፍትሔ ሐሳቦች ያካተተ ነው፡፡ በተለይም የድጋፍ ሰጪ የሥራ ክፍሉን አደረጃጀት በተመለከተ ይበል የሚያሰኝ እመርታ አሳይቷል ማለት ይቻላል፡፡ ቀሪዎችንም እንደ ነፃ የኦዲት ሥርዓት፣ ነፃ እና ጠንካራ የበጀት አደላደልና አወሳሰን ሥርዓት፣ ከውስጥ ገቢ የመጠቀም አሠራር፣ ነፃ የግዢና ንብረት ማስወገድ እንዲሁም ንብረት አስተዳደር ሥርዓትና ሌሎችንም ጉዳዮች በቀጣይ ሊያስብባቸው የሚገቡ መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡

የሕግ ማሻሻያዎቹ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቁ በኋላ፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በተደረጉት ማሻሻያዎች መሠረት አደረጃጀታቸውን በማስተካከልና ነፃና ገለልተኛ ፍ/ቤትን የሚመጥን መዋቅር በመዘርጋት በአዋጁ የተቀመጠውን ለውጥ በተግባር ማሳየትና ነፃነታቸውን ማስጠበቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተለይም፡-

ሀ) የፌደራል ፍርድ ቤቶች የድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎችን አስተዳደር በተመለከተ ለፍ/ቤቱ ደረጃ የሚመጥኑ ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ቅጥር፣ ምደባ፣ ዝውውር፣ ልማት፣ ዕድገት፣ ደመወዝና ጥቅማጥቅም እንዲሁም ማንኛውንም አስተዳደራዊ ጉዳዮችን አሁን አዲስ በተረቀቀው አዋጅ መሠረት ራሳቸው በሚያወጡት ደንብና መመሪያ መሠረት እንዲሆን ማድረግ፣

ለ) የፌደራል ፍርድ ቤቶች የበጀትና ፋይናንስ አስተዳደርን በተመለከተ በተረቀቀው አዋጅ መሠረት ከሀገሪቱ አጠቃላይ በጀት ላይ ጥቅል በጀት እንዲመደብ ለማድረግና በረቂቅ አዋጁ ላይ ባልተካተተውና ከላይ በምሳሌነት ለተገለፁት ተቋማት በተፈቀደው አግባብ መሠረት ፍ/ቤቶችም የውስጥ ገቢን እንዲጠቀሙ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ እንዲወጣ ማድረግ፣

ሐ) ፌደራል ፍ/ቤቶች የሚያስፈልጓቸውን ሎጂስቲክስ አቅርቦት ከአስፈጻሚው አካል እጅ ነፃ በሆነ መልኩ በራሳቸው እንዲገዙና ንብረቶችንም እንዲያስወግዱ የሚያስችል ሕግ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ፣

መ) ፌደራል ፍ/ቤቶች አሁን አዲስ በተረቀቀው አዋጅ መሠረት ራሳቸውን ችለው የሚመጥናቸውንና ጥራት ያለው ቀልጣፋ የዳኝነት አገልግሎት ለመስጠት

የሚያመች አደረጃጀት በማጥናትና በቀጥታ ለተወካዮች ምክር ቤት ወይም እንዳስፈላጊነቱና ተገቢነቱ ለዳኝነት አስተዳደር ጉባኤ በማቅርብና በማስጸደቅ ተግባር ላይ እንዲያውሉ ማድረግ፣

ሠ) ፌደራል ፍ/ቤቶች እንደማንኛውም ተቋም የአሠራር ሥርዓት ዘርግተው ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው ወጥ አካሄድ ለማስፈን የሚያስችሏቸውን መመሪያዎች ለማውጣት የሚያስችል ሥልጣን እንዲኖራቸው ማድረግ፣

ረ) እነዚህን ከላይ የተጠቀሱ መሠረታዊ ለውጦችና ሌሎች የዳኝነት ተቋማዊም ሆነ ግላዊ ነፃነቶችን ሊያስከብሩ የሚችሉ መርሆዎች የተካተቱበትና በአጠቃላይ የዳኝነት ሥርዓቱ ሊመራበት የሚችል የዳኝነት ፖሊሲ (Judicial policy) እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

ፌደራል ፍ/ቤቶቻችን በእውነትና በሕግ ላይ ተመሥርተው፣ ትክክለኛ፣ ጥራት ያለውና፣ ቀልጣፋ ዳኝነት በመስጠት የኅብረተሰቡን እርካታና አመኔታ (public satisfaction and trust) ያገኙ ተቋማት እንዲሆኑልን በምንመኘው መጠን፣ ይህን ተግባራዊ ማድረግ ቀላል ሥራ ባይሆንም የማይቻል ግን አይደለም፡፡ የዚህ አጭር ምልከታም ዋነኛ ዓላማ ሰፊና ጥልቅ የሆነውን የዳኝነት ነፃነት በሙሉ መዳሰስና ማብራራት ሳይሆን በተለይም የፌደራል ፍ/ቤቶች ተቋማዊና አስተዳደራዊ ነፃነት አሁን ላይ ምን እንደሚመስል፣ ምንስ መምሰል እንደሚገባው ያሉት የወደፊት ተስፋዎችና ተግዳሮቶች ምን እንደሆኑ ማመላከት ነው፡፡ እስከዛሬ ይህንን ርዕሰ-ጉዳይ መሠረት አድርገው የተጠኑት ጥናቶች በአብዛኛው (ምናልባትም በሙሉ በሚያሰኝ ሁኔታ) ያተኮሩት በዳኞች ግለሰባዊና ውሳኔያዊ ነፃነት ላይ ሲሆን፣ ተቋማዊና አስተዳደራዊ ነፃነታቸውን በተለይም ከሰው ኃይል አስተዳደርና ከበጀት ጋር በተያያዘ ሰፋ ባለ መልኩ ማጥናት እና ጉዳዩን በደንብ ማብሰል ለሚፈልጉ ተመራማሪዎችና ባለሙያዎች ይህ ጽሑፍ መንደርደሪያ ይሆናል ተብሎ ይገመታል፡፡ ■